# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## በማህበረሰብ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

በ

ልዩ ተዋበ

## ‹‹የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ከፊልም ጽሁፍ(ስክሪፕት) አላባውያን አንፃር››

ነሃሴ/2013 ዓ.ም

# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የማህበረሰብ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

በ

ልዩ ተዋበ

የጥናቱ አማካሪ

መ/ር ተመስገን ሽታዬ

ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

በማህበረሰብ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

ነሃሴ/2013 ዓ.ም

# የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በውልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቲያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማማያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገላት መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

የአማካሪው ስም ----------------------

ፊርማ -------------

ይህ ‹‹በተማሪ ልዩ ተዋበ››‹‹የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ከፊልም ጽሁፍ(ስክሪፕት)አላባውያን አንፃር›› በሚል ርዕስ የተሰራውን የመጀመሪያ ድግሪ ማሞያ ፁሁፍ ዩኒቨርስቲውን ጥራት ደረጃ ያሚላ እና ለቲያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው ፡፡ ይህም በፈታኝ ኮሚቴው ተረጋግጧል፡፡

ፈታኝ አንድ ስም______________________

ፊርማ _____________

ፈታኝ ሁለት ስም______________________

ፊርማ _____________

ቀን ---------------------------

# ምስጋና

በቅድሚያ ለዚህ ደረጃ ላደረሰኝ ለሥላሴ ክብርና ምስጋና ይሁንልኝ፡በመቀጠል ይሄን ጥናታዊ ጽሁፍ ስሰራ ምክር ሲሰጠኝ በሀሳብ ሲያግዘኝ ለነበረው መምህር ተመስገን ሽታዬ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ እዲሁም አይዞህ በርታ በማለት ሲያበረታቱኝ ለነበሩት ለእናቴ ሂሩት ሀይለማርያም ለወንድሜ አብነት ተዋበ እና ለጓደኞቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረስልኝ!!

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ተፈጣሪ ፊልምን ከፊልም ጽሁፍ አላባውያን አንጻር በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የፊልም ጽሁፍ አላባውያን ምን ምን እንደሆኑ ይቃኛል። እዲሁም የተፈጣሪ ፊልምን ከመቼት፣ ከገጸ-ባህሪ፣ ከቃለ-ፊልም፣ ከጭብጥ እና ከሴራ አንጻር በስፋት ይቃኛል። አጥኝው የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍን በመተንተን እንዲሁም ጠንካራ እና ደካማ ጎኖቹን ነቅሶ በማውጣት፣ ችግሮቹም መፍትሄ እንዲኖራቸው የራሱ ሀሳብ አስቀምጧል።

# ማውጫ

ምስጋና ........................................ i

አጠቃሎ ........................................ ii

ማውጫ ........................................ iii

ምዕራፍ አንድ ........................................ 1

1. መግቢያ ........................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 2

1.2 የጥናቱ ዓላማ ........................................ 2

1.2.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ ........................................ 2

1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ ........................................ 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 3

1.4 የጥናቱ ወሰን ........................................ 3

1.5 የጥናቱ ዘዴ ........................................ 3

1.5.1 የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ........................................ 4

1.5.1.1 መዛግብት ........................................ 4

1.6 የጥናቱ አወቃቀር ........................................ 5

1.7 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........................................ 5

ምዕራፍ ሁለት ........................................ 6

2.1.ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........................................ 6

2.2.የፊልም ምንነት ........................................ 6

2.3.የፊልም ፅሁፍ (እስክሪፕት) አላባውያን ........................................ 7

2.3.1.መቼት ........................................ 7

2.3.1.1 እውናዊ መቼት ........................................ 8

2.3.1.2. ሰው ሰራሽ መቼት ........ 8
2.3.2..ገፀ-ባህሪ ........ 9
2.3.2..1. ወጥ ገፀ-ባህሪያት ........ 10
2.3.2.2. አስተኔ ገፀ-ባህሪያት ........ 11
2.3.3.ግጭት ........ 11
2.3.4. ቃለ ፊልም ........ 12
2.3.5. ሴራ ........ 13
2.3.5.1. ልቅ (ልል) ሴራ ........ 14
2.3.5.2. ጥብቅ ሴራ ........ 14
2.3.5.3. ጥምር ሴራ ........ 15
2.3.5.4 ነጠላ ሴራ ........ 15
2.3.6. ጭብጥ ........ 16
2.3.6.1 አካባቢያዊ ጭብጥ ........ 17
2.3.6.2 አለም አቀፋዊ ጭብጥ ........ 17
**2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 24**
3. የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ጭምቅ ታሪክ ........ 24
3.1 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ትንተና ከፊልም ጸሁፍ (ስክሪፕት) አላባውያን አንጻር ........ 26
3.1.1. የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ መቼት ........ 26
3.1.1.1 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ከእውናዊ መቼት አንጻር ........ 28
3.1.1.2 የተፈጣሪ ፊልም ጽኑፍ (እስክሪፕት) ከሰው ሰራሽ መቼት አንጻር ........ 29
3.1.3 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ከግጭት አንጻር ........ 29
3.1.3.1 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ግጭት ሰው ከሰው ጋር ........ 34
3.1.3.2. የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ግጭት ሰው ከፈጣሪ ወይም ከእጣፈንታ ጋር ... 37
3.1.4 የተፈጣሪ ፊልም (ጽሁፍ (ስክሪፕት) ከቃለ ፊልም አንጻር ........ 38
3.1.5 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ከሴራ አንጻር ........ 41
3.1.6. የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ከጭብጥ አንጻር ........ 42

4.1. ማጠቃለያ ........................................................................................................ 44

4.2 የመፍትሄ ሀሳቦች ................................................................................................ 45

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ፊልም በአይን የሚታይ አንዱ የጥበብ ዘርፍ ነው ። በካሜራ አማካኝነት የተቀረጸ የተንቀሳቃሽ ምስሎች ስብስብ ነው ።

ዘላለም ተፈሪ "የፊልም ትወና ጥበብ " በተሰኘው መፅሐፉ ስለ ፊልም ከዚህ በታችይ አስፍሮታል።

> የፊልም ጥበብ በተንቀሳቃሽ ምስሎች አማካኝነት ለተደራሲያን ታሪክ የሚነገርበት እና መልዕክት የሚተላለፍበት የሰው ልጆች ኪነጥበባዊ የተግባቦት መንገድ ነው ።አብዛኛውን ጊዜ ታሪኩ የሚነግረውበድርጊ ትና በምስል ላይ ተመስርቶም ስለሆነ የፊልም ጥበብ ዕይታዊ ጥበብ ነው ማለት እንችላለን ።(1010፧18)

ፊልም የዕይታ ጥበብ ሲሆን በዚያም ውስጥ ታሪክ ፣ ገፀባህሪ ፣ መቼትን የመግለጽ አቅም አለው ። የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ብዙ የህይወት ውጣ ውረዶች ገጠመኞች ይኖሩታል ። እነዛን ስሜቶቹን የሚገልጽበት ለሰዎች የሚያጋራበት ብዙ መንገዶች ሲኖሩት ፊልም ከነዛ መካከል አንዱ ነው ። እንዲሁም ፊልም ያለፈን ታሪክ ቀርፆ በማስቀመጥ ለትውልድ የሚያስተላልፍ ወይም የሚነግር የጥበብ ዘርፍ ነው ፧ እንዲሁም የገሀዱን አለም እውነታ በምስል ያሳየናል ።

ጳውሎስ አዕምሮ "የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ " በተሰኘው መፅሐፉ ስለ ፊልም ከዚህ በታች አስፍሮታል ።

> የዕይታ ጥበብ የሆነው ፊልም የተለያዩ ምስሎችን በተንቀሳቃሽ መቅረፅ ምስልን ወይም ካሜራን በመመዝገብ የሚሰጥ እረቂቅ የኪነ ጥበብ ነው ። ይህ የኪነ ጥበብ ዘርፍ በውስጡም ምስልን ፣ ድምፅን ፣ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን በማቀነባበር የዕይታን ምትሃት በግብአት አማካኝነት በመፍጠር ተደራሲያንን

በሚያዝናና ፣ በሚያስተምር እና በሚያስገርም መልኩ እንዲቀርብ ያደርጋል ፡፡
ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በምስል ማሳያ አማካኝነት እንዲታዩ በሚያደርግበት
ወቅት የምንመለከተው እንቅስቃሴ ልክ በገሀዱ ዓለም የምናየው ድርጊት
ይመስላል ፡፡ (2010፤9)

ፊልም ታሪክን በምስል ፣ በእንቅስቃሴ እና በድርጊት ቅንብር የመግለጽ ጥበብ ነው ፡፡ ፊልም ታሪክን ፣ ሁኔታዎችን መንገር ብቻ ሳይሆን በምስል በማሳየት ታሪክ መንገሪያ መንገድ ነው ፡፡

አንድ ፊልም ሲፃፍ የተሟላና የተሳካ ለመሆን የፊልም ፅሁፍ አላባውያንን በተገቢው መንገድ ማካተት አለበት ፡፡ የፊልም ፅሁፍ አላባውያን የምንላቸውም መቼት ፣ ገፀባህሪ ፣ ግጭት ፣ ቃለ ፊልም ፣ ሴራና ጭብጥ ናቸው ፡፡ አንድ የፊልም ፅሁፍ የተሟላ ሆኖ እንዲቆም የፊልም ፅሁፍ አላባውያን ድርሻቸው ከፍተኛ ነው ፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚው "የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍን ከፊልም ፅሁፍ አላባውያን አንፃር " አጥንቷል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አጥኚው ይህን የተፈጣሪ ፊልም ስክሪፕትን ከፊልም ፅሁፍ(ስክሪፕት) አላባውያን አንፃር ይዳስሳል፡፡ ይህን ጥናት ለመስራት የተነሳሳበት ምክንያት አጥኚው በዳሰሳ ከተመለከታቸው የሀገራችን ፊልም ፅሁፎች መካከል የፊልም አላባውያንን ከመጠቀም አንፃር አላባውያኑን በሚገባ ማሳየት በመቻሉ ነው ፡፡ በተጨማሪም የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ በአፃፃፍ ቴክኒኩ ለየት ያለ በመሆኑ ፅሁፍን ከፊልም ፅሁፍ አላባውያን አንፃር ለማየት ካደረበት ከፍተኛ ፍላጎት ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በውስጡ አብይና ንዑስ አላማዎች አሉት ፡፡

## 1.2.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ "የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍን ከፊልም ፅሁፍ አላባውያን አንፃር" ትንታኔ ማቅረብ ነው ፡፡

## 1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

- የፊልም ፅሁፍ አላባውያንን ማብራራት

- የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍን ከፊልም ፅሁፍ አላባውያን አንፃር ተመልክቶ ትንታኔ መስጠት

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

- ከአጥኚው ጋር ተመሳሳይ እርስ ላላቸው አጥኚዎች እንደ መረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል

- ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል "ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ"ማሟያነት ያገለግላል

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ወሰን የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍን ከፊልም ፅሁፍ አላባውያን አንፃር " በመፈተሽና በመተንተን ላይ የተገደበ ነው ። ጥናታዊ ፅሁፉም በዋናነት ገፀባሕርያት አሳሳል ፣ ግጭት ፣ ሴራ ፣ መቼት ፣ ቃለ ፊልም እንዲሁም ጭብጥ ላይ የተወሰነ ነው ።

## 1.5 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ "ገላጭ ምርምር "(Discriptive) የአጠናን ዘዴን ተጠቅሟል ።ይህ የምርምር ዘዴ አንድን ነገር ምንድነው ብሎ የሚጠይቅ ወይም ጥያቄዎችን በማንሳት እና የሚያነሳውን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የሚሰራ የምርምር አይነት ነው ።

አለም እሸቱ "የምርምርና ዘገባ አፃፃፍ ዘዴ" በሚለው መፅሐፉ ላይ ስለ ገላጭ ምርምር ዘዴ እንደሚከተለው አስፍሮታል ።

"ገላጭ ምርምር ገለፃን ፣ ትንታኔንና አተረጓጎምን መሰረት የሚያደረግ ሲሆን በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚኖረውን ተዛምዶ እያወዳደረና እያነፃፀረ ሊመለከት ይችላል ። በዚህ ሂደት ውስጥ መረጃዎችን ከተለያየ ምንጭ የሚያሰባስብ ሲሆን ትኩረቱን ግን የአንዱን ተጨባጭ ሁኔታ ትክክለኛ ባህሪ መግለጽ ወይም ማሳወቅ ይሆናል ።(1994፤148-149)

ገላጭ የምርምር አይነት ገለፃና ትንታኔ ላይ በይበልጥ መሰረት የሚያደርግ የጥናት አይነት ነው ።ይህም ጥናት ትኩረት የሚያደርገው "የተፈጣሪ ፊልም ከፊልም ፅሁፍ አላባውያን አንፃር" የፊልም ፅሁፍ አላባውያንን በምን መልኩ ተጠቅሟል የሚለውን አንብቦ በመተንተን ላይ ስለሆነ የጥናቱ ዘዴ ገላጭ ነው ለማለት ይቻላል ።

### 1.5.1 የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ

አንድን ጥናት በምንሰራበት ወቅት የተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶችን ልንጠቀም እንችላለን ። ፕሮፌሰር ያለው እንዳወቀ "የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር" በሚለው መፅሐፉ ስለመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች እንደሚከተለው አስፍሯል ።

> በምርምር ሂደት እንደ ምርምሩ አይነት ፣ እንደ ተጠኝዎቹ ሁኔታ ፣ እንደ ተመራማሪው ችሎታ ፣ተመራማሪው ምርምሩን ለማካሄድ እንዳለው የገንዘብና የጊዜ መጠን፣የስልጠናና የፍልስፍና ሁኔታ ለመረጃ ማሰባሰቢያነት የሚያገለግሉ በርካታ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች አሉ። ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። 1 የፅሁፍ መጠይቅ
>
> 2 ቃለ መጠይቅ
>
> 3 ምልከታ
>
> 4 መዛግብት
>
> 5 የተለያዩ ፈተናወች
>
> 6 ቡድን ተኮር ውይይት (2009፤147-148)

ጥናት ለመስራት ሲታሰብ ጥናቱ በምን አይነት ዘዴ እንደሚሰራ መታወቅ አለበት ። ያም እንደ ጥናቱ እርስ ወይም አይነት ይወሰናል ። በዚህም መሰረት አጥኚው ይህን ጥናት የሚሰራበት መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ መዛግብት ነው ።

#### 1.5.1.1 መዛግብት

መዛግብት አንድ ጥናት አድራጊ ጥናቱን በሚያደርግበት ወቅት አገላብጦ የሚያያቸው ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው መፅሃፍት ፣ ጋዜጣ የተለያዩ የሚነበቡ መዝገቦችን ተጠቅሞ መረጃ የሚያገኝበት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ነው ። ፕሮፌሰር ያለው እንዳወቀ "የምርምር መሠረታዊ መርሆች እና አተገባበር" በሚለው መፅሐፉ ስለ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች አንዱ ስለሆነው መዛግብት ከዚህ በታች እንደሚከተለው አስፍረዋል *።"መዛግብት ተመራማሪው ስለ*

*አለፈም ይሁን ስለ ወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለማሰባሰብ ሲነሳ ሊጠቀማቸው የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው ። መዛግብት በፅሁፍ መልክ ከየቤተመፅሀፍቷ ፣ ቤተመዛግብቱ ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎችና እንደሁኔታውም ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው።" (2009፤191)*

በዚህም መሠረት አጥኚው ይሄን ጥናት በዋነኝነት የሚሰራው በተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ላይ በመሆኑ እና የሚጠቅማቸውም የመረጃ ምንጮች መፅሀፍትና ተነባቢ ነገሮች በመሆናቸው ይሄን የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴን ለመምረጥ ችሏል ።

## 1.6 የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናት በተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ላይ ብቻ የተገደበ ሲሆን በአራት ክፍሎች ወይም ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው ። ምዕራፍ አንድ ፤ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ ዓላማ ፣ የጥናቱ ዋና ዓላማ ፣ የጥናቱ ንዑስ ዓላማ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ፣ የጥናቱ አወቃቀርና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦች ይይዛል ። በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝትና የንድፈ ሀሳብ ቅኝት የፊልም ፅሁፍ አላባውያን የሚባሉት መቼት ፣ ገፀባህሪ ፣ ቃለ ፊልም ፣ ሴራ ፣ ግጭት እና ጭብጥን ይይዛል ። በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ጭምቅ ታሪክ እና በምዕራፍ ሁለት ከተቀመጡት የፊልም ፅሁፍ አላባውያን አንፃር እንዴት እንደተተገበሩ እና ምን መምሰል እንደነበረባቸው ትንታኔ የሚሰጥበት ክፍል ነው ። የመጨረሻውና አራተኛ ምዕራፍ ማጠቃለያ ፣ የመፍትሔ ሀሳቦች ፣ ዋቢ መፅሐፍት ፣ አባሪ ፣ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው የሚቀርቡበት ይሆናል ።

## 1.7 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- የፊልም ምንነት ?

- የፊልም ፅሁፍ ምንነት ?

- የፊልም ፅሁፍ አላባውያን ምንነት ?

- የፊልም ፅሁፍ አላባውያን እዚህ ስክሪፕት ላይ እንዴት ተተገበሩ?

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የፊልም ምንነት

ፊልም ማለት በተንቀሳቃሽ ምስል አማካኝነት የሚከናወን ጥበብ እና በሲኒማ እስክሪን የሚቀርብ የጥበብ አይነት ነው፡፡ እንዲሁም ደራሲው በገሀዱ አለም የሚያየውን እና ከዚህም በኋላ ይመጣል ወይም ሊከሰት ይችላል ብሎ ያሰበውን በማካተት በምዕናብ የሚፈጥራቸው ገፀ-ባህርያት አማካኝነት ታሪካዊ ወይም ሰው ሰራሽ የሆነ መቼት በመጠቀም የሚያሳይበት መንገድ ነው፡፡

ዘላለም ተፈሪ ‹‹የፊልም ትወና ጥበብ›› በተሰኘው መፅሀፉ ስለፊልም ምንነት ከዚህ በታች አስፍሯል፡፡

> *የፊልም ጥበብ በተንቀሳቃሽ ምስሎች አማኝነት ለተደራሲያን ታሪክ የሚነገ ርበት እና መልዕክት የሚተላለፍበት የሰው ልጆች ኪነ-ጥበባዊ የተግባቦት መንገድ ነው አብዛኛውን ግዜ ታሪኩ የሚነገረው በድርጊትና በምስል ላይ ተመስርቶ ስለሆነ የፊልም ጥበብን እይታዊ ጥበብ ነው ማለት እንችላለን፡፡(2010፣18)*

የፊልም ጥበብ የሚቀርበው በ‹‹እስክሪን›› ውስጥ በመሆኑ ይበልጥ ምስል ከሳች እና ለገሀዱ አለም የቀረበ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ፊልም በድምፅ ከመስማትም ባለፈ በአይንም ጭምር የሚታይ የዕይታ ጥበብ በመሆኑ በአይናችን በማየት ብቻ (ቋንቋ ሳይገድበው) ለመመልከት ያስችላል፡፡

ይህ ዘርፍ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ለማስተማር፣ ለማዝናናት፣ ለማነሳሳት ተግባራት ይውላል፡፡ በእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተሰርቶ በሲኒማ የሚታይ ተንቀሳቃሽ ምስል፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ግንኙነት ለመፍጠር ያስችለናል፤በአይን የሚታይ እና በድርጊት የሚገለፅ በመሆኑ የቋንቋ መወሰን ሳይገድበው ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችል የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡

> *ፊልም ታሪክን በማስተላለፍ እና የሰዎችን ስሜት በማነሳሳት (በመቀስቀስ) ውጤታማ የሚዲያ አይነት ነው፡፡ የተንቀሳቃሽ ምስች ሰብሰብ ሲሆን ከሌሎች የጥበብ ስራዎች በተለየ ብዙ ‹‹ቴክኒኮችን››*

*የሚፈልግ ነው። ከነሱም መካከል በድምፅ ቀረፃ፣የምስል ቀረፃ እና የብርሀን ቴክኒኮችን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። (www. Britannica.com)*

ፊልም በባህሪው ለእውነታው አለም የቀረበ በመሆኑ፣በምስል፣በብርሀን፣በድምፅ ስለሚታገዝ፣ በቀላሉ ከሰዎች ስሜት ጋር መቆራኘት ይችላል። በዛም ውስጥ ታሪክን ፣ መንገር፣ መላዕክትን ማስተላለፍ፣ ማነሳሳት፣ ይችላል።

## 2.2.የፊልም ፅሁፍ (እስክሪፐት) አላባውያን

### 2.2.1 መቼት

*መቼት ከስሙ መረዳት እንደምንችለው መቼና የት የሚሉት ቃላት ውህድ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን። በፊልሙ ውስጥ የሚታየው ድርጊት የተካሄደበትን ቦታና ጊዜ እንዲሁም ማህበራዊ ሁኔታን የሚያሳየን አንዱ የፊልም ፅሁፍ (እስክሪፐት) አላባ ነው።*

*ኤልያስ ጋሻው ‹‹ ስኬታማ የፊልም አሰራር ከመደበኛ ህግጋት ባሻገር ›› በተሰኘው መፅሀፉ ስለ መቼት እንደሚከተለው አስፍሯል።*

> *ታሪኩ የሚፈፀምበት አካባቢ (ቦታ) በፊልሙ ውስጥ የተጨባጭ አላማ ምሳሌ (መገለጫ) ነው። በፊልም ድርሰት ውስጥበተለያዩ ዝርዝር መገለ ጫዎችመግለፅ አለበት። የታሪክ ተቀባይነት በገፀ-ባህርያት ምልልስ ታአማኒነትና በግዜ እና ቦታዎች አሳማኝ መሆን ላይ የተመሰረተ ነው። ተመልካች አችን ያንን ሰውዬ የሆነ ቦታ አውቀዋለሁ እዛ ቦታ አንድ ወቅት ነበርኩ የሚል ስሜት እንዲፈጥር ያደርገዋል።*
>
> (2007፣6-8)

*የአንድ ፊልም ፅሁፍ (ስክሪኘት ) መቼት ታሪኩ የሚፈፀምበትን ቦታ እና ግዜ በራሳችን ሂወት የሆነ ወቅት ላይ የምናቀው ወይም የኖርንበት እስኪመስለን ድረስ እንዲሰማን ያደርገናል። እንደዚሁም የምንጠቀመው ቦታ የተመልካቹ አዕምሮ ላይ ተቀባይነትን መፍጠር ያስችለዋል።*

*መቼት አንድ ታሪክ የሚተረክበት ቦታ ጊዜ እና ማህበራዊ እውነት ነው። ካለን የታሪኩን መቼት ሊገለፅ የሚችል አንድም በደራሲው ምዕናብ በተፈበረከው ትክክለኛ ቦታዎችን የመቼት*

ገለፃዎችን አልፀም ደሞ የገሀዱ አላማ እውነታ መሆኑን የተፈጥሮ መቼትን በመጠቀም ነው፡፡ በዚህም መሰረት ፈንታሁን እንግዳ ‹‹የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ›› በሚለው መፀሀፍ መቼትን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ እንደሚከተለው  አስፍሯል፡፡

> መቼት ተፈጥሮአዊ (እውናዊ) እና ስነ-ፅሁፋዊ (ሰው ሰራሽ) ተብሎ ሊከፈል ይችላል የተፈጥሮ መቼት በየብስ፣በውቅያኖስ እና በሰማይ ላይ የሚገኙትን መልከአ ምድራዊ  ትዕይንቶችን እና የግዜ ክስተቶችን ለምሳሌ የቀንና የሌ ሊት የበጋና የክረምት መፈራረቅን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡(2009፣12)

## 2.2.1.1. እውናዊ መቼት

በገሀዱ አለም ያለውን የሰው እንቅስቃሴ፣እምነት፣አስተዳደግ፣አለባበስ ማህበራዊ እውነታንና የእንሰሳት አኗኗር ሁኔታ እንደዚህም ተፈጥሮአዊ ገፅታ አቀማመጥና ሂደት እውነት ባለው መልኩ የሚያቀርብ ተፈጥሮአዊ መቼት ነው፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ›› በተሰኘው መፅሀፉ ‹‹የተፈጥሮ መቼት በየብስ፣ በውቅያኖስና በሰማይ ላይ የሚገኙትን መልከአ ምድራዊ ትእይንቶችንና የጊዜ ክስተቶችን ለምሳሌ የቀንና የሌሊት፣ የበጋና የክረምት መፈራረቅን ሁሉ ያጠቃልላል››፡፡ (2009፣12)

## 2.2.1.2. ሰው ሰራሽ መቼት

የተጋነኑና ተፈጥሮአዊ ያልሆኑ መቼቶች ነገር ግን በደራሲው ወይም በአዘጋጁ አዕምሮ በምናብ ተስለው የሚቀርቡና ተመልካችን በማዝናናት የሚዘጋጁ የፈጠራ አይነቶች ናቸው፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ ›› በተሰኘው መፅሀፉ ስለ ሰው ሰራሽ መቼት ምንነት እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ሰው ሰራሽ ተውኔታዊ ወይም ስነ-ፅሁፋዊ መቼት እንደ ተፈጥሮአዊ መቼት ልቅና ግርድፍ ሳይሆን የተመረጠና የተወሰነ አቀራረብ ብቻ ይኖረዋል፡፡ደራሲያን የፈጠሯቸው ገፀ-ባህሪያት የሚያከናውኑትን ድር ጊት በየትኛውም ቦታ ጊዜ እና ሁኔታ እንደሚያከናውኑ ተፈጥሮአዊ በሆነ እና በተንዛዛ መልኩ ሳይሆን ከምዕናባዊ ፈጠራ የተመረጡ የመ ቼት ገለፃዎችን ብቻ ያቀርባሉ፡፡ (2009፣12)

ሰው ሰራሽ መቼት ባህሪው ልክ እንደ ተፈጥሮአዊ መቼት በሰፍ እና የተንሰራፍ አይሆንም የተመጠነ እና የተወሰነ ሆኖ ነው የሚቀርበው፡፡ ደራሲው በምዕናቡ በሳለው አለም ውስጥ ታሪኩን ያጠናቅቃል፡፡

### 2.2.2 ገፀ-ባህሪ

ገፀ-ባህሪ በድርሰቱ ውስጥ ደራሲው በምዕናቡ የፈጠራቸው ፍጥረታት ናቸው ሰው ሊሆን ይችላል የማይናገሩ፣የማይንቀሳቀሱ ነገሮችን እንዲናገሩ፣ እንዲንቀሳቀሱ ተደርገው ሊቀርቡም ይችላሉ፡፡ ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ ተውኔታዊ መዝገብ ቃላት እና ፍቻቸው›› በሚለው መፅሀፍ

‹‹ገፀ-ባህሪ በተውኔት፣በልብ ወለድ እና በተራኪ ግጥም ተስሎ የሚገኝ የድርሰቱ ሰው ነው፡፡ የድርሰቱ ሰው ስንል ሰብአዊ ፍጡርን፣ እንሰሳትን፣ ረቂቅ የሀሳቦችን ሰማያዊ ፍጡርን እና መናፍስትን፣ ይጨምራል››፡፡ (2012፣2260

ገፀ-ባሪያት ካላቸው ሚና አንፃር የተለያዩ ደረጃና ክፍል ይኖራቸዋል፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ የተውኔት ድርስት አፃፃፍ ዘዴ›› በተሰኘው መፅሀፍ ስለ ገፀ-ባህሪ ሚና አሰጣጥ እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

ገፀ-ባህሪያት በውስብስብ ባህሪያቸው እና በታሪኩ ውስጥ ከሚሰጣቸው ሚና አንፃር በሚከተለው መልኩ ከፋፍለን አስቀምጠናቸዋል፡፡

- ወጥ ገፀ-ባህሪያት እና አስተኔ ገፀ-ባህሪያት
- ሰናይ ገፀ-ባህሪያት እኩይ
- ደብቅ ገፀ-ባህሪያት ግልፅ
- አብይ ገፀ-ባህሪያት ንዑስ
- ታሪካዊ ገፀ-ባህሪያት ምናባዊ
- አዳጊ ገፀ-ባህሪያት ቆምቀር

በማለት መከፋፈል ይቻላል፡፡ (2009፣16)

ከላይ የተጠቀሱትን በሙሉ አጠቃለው የሚይዙት ወጥ ገፀ-ባህሪያት እና አስተኔ ገፀ-ባህሪያት ናቸው፡፡

## 2.2.2.1 ወጥ ገፀ-ባህሪያት

ወጥ ገፀ-ባህሪ ማለት ታሪኩን በዋናነት ተሸክሞ ከመጀመሪያው አንስቶ አስከ መጨረሻ ድረስ የሚዘልቅልን እንዲሁም የታሪኩ መሰረት ነው፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ›› በሚለው መፅሀፍ ስለ ወጥ ገፀ-ባህሪ እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ወጥ ገፀ-ባህርያት ከምንም ከምንም በፊት ምንነታቸው ለአንባቢም ሆነ ለተመልካች ይፋ የሚሆነው በመጀመሪያው የገፀ-ባህሪያት የአሳሳል ደረጃ ማለትም በነፍስ ወክፍ አካላዊ አቋማቸው ደረጃ የእያንዳንዱ ገፀ-ባህሪ አለባበስ ፆታ፣ዕድሜ፣እንቅስቀሴ፣ጤና፣ድምፅ፣መልክ፣ አቋምን ማለትም ውፍረት፣ቅጥነት፣እርዝመት፣እጥረት፣ምን እንደሆነ ያብራራል፡፡(2009፣17)

አካላዊ ገለፃ ብዙ የተወሳሰበ ገፀ-ባህሪ ገለፃ አይደለም፡፡ የካረክተሩን በአይን የምናየው ማንነቱን የሚገልፅልን፣ ቁንጅናን ሊሆን ይችላል፡፡ ማስፈራትን ከለርን ማጠርን መርዘምን ወዘተ… የሚገልፅልን የገፀ-ባህሪ አሳሳል አይነት ነው፡፡

ወጥ ገፀ-ባህሪያት የትኛውም ድርጊት በሂወታቸው ወሳኝ የሚባል ተፅዕኖ አያደርግም፡፡ የሠው ልጅ ሊሸከመው የማይችል ሀዘን ቢደርስባቸውም ወይም ደሞ በተቃራኒው የሚያስጨፍር ደስታ ቢያጋጥማቸውም ሂወታቸውን ወይም አቋማቸውን አይቀይረውም፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔያቸው›› በሚለው መፅሀፍ ስለ ወጥ ገፀ-ባህሪ እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ይህ ገፀ-ባህሪ አንዳንድ ጊዜ ባለ አራት መልክ ባለ አራት ገፅ እና ባለ አራት መጠነ ርዕሰ ገፀ-ባህሪ በመባል ይጠራል፡፡ ወጥ ገፀ ባህሪ አካላዊ፣ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ግብረ ገባዊ መልኩ ሁሉ ጥልቀት ባለው መንገድ እና ግልጥልጥ ባለ ሁኔታ ተስሎ የምናገኘው የገፀ-ባህሪ አይነት ነው፡፡(2012፣163)

ወጥ ገፀ-ባህሪ ከሌሎች አስተኔ ገፀ-ባህሪያት በተሻለ መልኩ፣በአካላዊ ፣ማህበራዊ፣ስነ-ልቦናዊ እና ግብረ ገባዊ በሆነ መልኩ ተስለው እንመለከታለን፡፡ ወጥ ገፀ-ባህሪ የተውኔቱ ዋና ወይም ተውኔቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ድርሰቱ ላይ ወይም ተውኔቱ ውስጥ የሚቆይ የገፀ-ባህሪ አይነት በመሆኑ በደንብ በተዋቀረ መልኩ ይሳሳል፡፡ አካላዊ የገፀ-ባህሪ አሳሳል ገፀ-ባህሪው ያለውን አቋም መልክ በአይን የሚታዩ አካላትን ሲገልፅ፣ማህበራዊ ደሞ ገፀ-ባህሪው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን (ሶሻል ላይፍ) ማህበራዊ ኑሮ የሚያሳይ ለምሳሌ

ስራው፣ያገባ፣ያላገባ፣በማህበረሰቡ ጋር ያለው መስተጋብር፣ የሀብት ደረጃ...ስነልቦናዊ፣ገፀ-ባህሪው ምን ይወዳል፣ምን ይጠላል፣ተስፋው ምንድነው? የሚፈራው ምንድ ነው?፡፡ ግበርገባዊ የገፀ-ባሪያችን ፀባይ፣ቁጡ፣ሳቂታ፣ቀዥቃዣ፣የተረጋጋ፣እነዚህን ይገልፃል፡፡ ወጥ ገፀ-ባህሪ በነዚህ በአራቱ የገፀ-ባህሪ አሳሳል በደንብ የተቃኘ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 2.2.2.2. አስተኔ ገፀ-ባህሪያት

አስተኔ ገፀ-ባህሪ በአግባቡ ላይሳል (ላይገለፅ) የሚችል በታሪኩ ውስጥ ዋና የማይባል ትንሽ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ›› በሚለው መፀሀፍ ስለ አስተኔ ገፀ- ባህሪ ከዚህ በታች እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ምን ጊዜም በተውኔትም ሆነ በልብ ወለድ ድርሰቶች ውስጥ በጣም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ወጥ ገፀ-ባህሪያት ሲገኙ ቁጥራቸው ከጣት ቁጥር የበዙ አስተኔ ገፀ-ባህሪያት መገኘታቸው የተለመደ እና የሚጠበቅም ነው፡፡ አስተኔ ገፀ-ባሪያት በቁጥር ይብዙ እንጂ በየፈጠራ ድርሰቱ ታሪክ ውስጥ የሚሰጣቸው የተሳታፊነትድርሻ ትንንሽ ከመሆን አልፎ በአካልም ሆነ በግብር ሳይገኙ በስም ብቻ ተጠቅሰው የሚታለፉበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ (2009፣30)

አስተኔ ገፀ-ባህሪያት ምንም እንኳን በድርሰቱ የሚፈጥሩት ሚና በአፃራዊነት ትንሽ ቢሆንም ነገር ግን በአንድ ድርሰት ውስጥ በቁጥር ብዙ የሆኑ አስተኔ ገፀ-ባህሪያት ይኖራሉ፡፡ አስተኔ ገፀ-ባህሪያት በሴራው ውስጥ ያሉ ድርጊቶች ስብዕናቸውን ውስጣዊ/ውጫዊ ማንነታቸውን የማይለውጡ እና ሌላ አመለካከት የማይዙ ናቸው፡፡

### 2.2.3. ግጭት

ግጭት በድርሰቱ /በፊልም ስክርፕቱ/ ገፀ-ባህሪያት መካከል የሚፈጠር አለመግባባት ነው፡፡

ጀስቲን ካሽ ‹‹ የድራማ አላባውያን›› በሚል ርዕስ የፃፈው ፅሁፍ ላይ ስለ ግጭት ከዚህ በታች አስፍሯል፡፡

> ግጭት በሁለት ይከፈላል፡፡ ውስጣዊ ግጭት እና ውጫዊ ግጭት ናቸው
>
> ውስጣዊ ግጭት
>
> - ሰው- ከራሱ ጋር
>
> ውጫዊ ግጭት

- ሰው - ከፈጣሪ ጋር /ከእጣፈንታ/
- ሰው- ከሰው ጋር
- ሰው- ከማህበረሰቡ ጋር
- ሰው- ከተፈጥሮ ጋር
- ሰው- ከቴክኖሎጂ ጋር (2016፣1) 1

የሰው ልጅ በዕለተዕለት እንቅስቃሴው ውስጥ ብዙ ነገሮች ያጋጥሙታል፡፡ የሚያጋጥመውን ነገር ሁሉ የሰው ልጅ አዕምሮ ላይቀበለው ይችላል በዚያም ምክንያት የተለያዩ ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡

ኤልያስ ጋሻው ‹‹ ስኬታማ የፊልም አሰራር ከመደበኛ ህግጋት ባሻገር›› በሚለው መፀሃፍ ስለ ግጭት እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ግጭት በፊልም ታሪክ ውስጥ መዓካላዊ እና መሰረታዊጉዳይ ነው፡፡ሰው ከሰው ጋር፣ ሰው ከአካባቢው ጋር ሰው ከራሱ ጋር የሚዳረጉ ግጭቶች በነባሩ ፊልሞች ውስጥ የተለመዱ ናቸው፡፡ የእድሜ፣ የፆታ፣ የሀይማኖት የባህል ወዘተ… ልዩ ነቶች ለግጭቶች መነሻ ናቸው፡፡ ሁለት ተፃራሪ ጫፎች ወይምተቃራኒ ሁኔቶች ሀሳቦች፣ድርጊቶች፣አቋሞች፣ወዘተ.. ለግጭት መነሻ ናቸው፡፡ለምሳሌ ፖሊስ እና ወንጀለኛ፣ አቃቤ ህግና ወንጀለኛ ሀብታምና ደሀ፣በጀግና እና ከተቀናቃኝ መካከል የሚደረጉ ግጭቶች በዋነኞቹ የነበሩ የምዕራባዊ ዘውግ ፊልሞች የግጭት መገለጫዎች ናቸው፡፡ (2007፣10)

ግጭት ለአንዱ ፅሁፍ(ስክሪፕት) በጣም አስፈላጊ እና መሰረታዊ የሆነ አላባ ነው፡፡ ብዙውን ግዜ ግጭት የሚፈጠረው በተለያዩ ወይም ተቃራኒ በሆኑ ነገሮች መካከል ነው፡፡

### 2.2.4. ቃለ ፊልም

ቃለ ፊልም በድርሰቱ፣ በተውኔቱ ወይም በልቦለድ ስራዎች ውስጥ መቼትን ለመግለፅ፣ሴራን ለማራመድ፣ገፀ-ባህሪያትን ለማስተዋወቅ፣የገፀ-ባህሪያትን እርስ በእርስ ግንኙነት ለማሳየት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ኤልያስ ጋሻው ‹‹ ስኬታማ የፊልም አሰራር ከመደበኛው ህግጋት ባሻገር›› በሚለው መፀሃፍ ስለ ቃለ ፊልም እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ምልልስ የገፀ-ባህሪን ታአማኒነትና ተቀባይነት ይወስናል ምልልስ ሴራውን ለማዳበርና ለማራመድ ወይም ገፀ-ባህሪን በውጤታማነት ለመቅረፅ

> ሲውል ሁልጊዜም ታአማኒነት ያለው ሊሆን ይገባል ይህም በፊልም ውስጥ የገሀዱን አለም ሰዎችን ባህሪና አቋም ይዘው መገኘት አለባቸው፡፡(2007፣4)

አንድ ገፀ-ባህሪ በሚናገረው ንግግር ወይም ቃለ ፊልም ብቻ ስለሱ ማንነት ለማወቅ ያስችላል፡፡ እንደዚሁም በተውኔቱ ውስጥ ቃለ ፊልም ተውኔቱ እንዲጎዝ እንዲቀጥል ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ቃለ ፊልም ገፀ-ባህሪያት ካላቸው ስብዕና ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት ይህም ሲባል ገፀ-ባህሪያት ከሚኖሩበት ማህበራዊ እውነታ እና በአካባቢያቸው ባለ ዘዬ፣ከእምነታቸው፣ ከአቋማቸው ጋር የተመሳሰለ የተዋሀደ መሆን አለበት፡፡

### 2.2.5. ሴራ

ሴራ በምክንያትና ውጤት የተሳሰረ የድርጊት ቅደም ተከተል ነው፡፡ የአንድ ነገር መፈጠር ላለፈው ነገር ውጤት ለሚመጣው ወይም ለቀጣዩ መነሻ (መንስኤ) እየሆነ እና አሳማኝ በሆነ ምክንያት እየተሳሰረ ሲሄድ ሴራ ይባላል፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ የተውኔት አዊ መዝገብ ቃላት እና ብያኔአቸው›› በተሰኘው መፀሀፍ ስለ ሴራ እንደሚከተለው አስፍሮ ይገኛል፡፡

> ሴራ አፅመ ታሪክ እና ትልም በሚሉት መጠሪያዎችም ይታወቃል፡፡ የተውኔት ወይም የልብ ወለድ ድርጊቶች በቅደም ተከተል የሚቀርብበትን ክዋኔ ያሳያል፡፡ ሴራ፣ ገፀ-ባህሪ፣እና ግጭትን በዋናነት ይይዛል፡፡ የተውኔትን ወይም የልቦለድን አጠቃላይ ሴራ መናገር ማለት ገፀ-ባህሪያት እንዴት በመጀመሪያ ግጭትጀምረው እንዴት እንደሚያከሩት ከዚህም እንዴት መፍትሔ እንደሚያገኙለት በመናገር ማለት ነው፡፡(2012፣ 81)

ምክንያት ያለው ድርጊት ሌላ ምክንያት ኖሮት ወደ ሌላ ድርጊት ሲሻገር ሴራን ይፈጥራል፡፡ ሴራ በቅደም ተከተል የተዋቀረ ነው ሲባል ነገሮችን እንዲያው በደፈናው ይደረድራል ማለት አይደለም፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ›› በተሰኘው መፀሀፍ ስለ ሴራ አይነቶች እንደሚከተለው አስፍሮ ይገኛል፡፡

> ከሴራ አይነታቸው አንፃር የተውኔት ዘውጎች፣በአራት ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡
>
> - ባለ ልቅ (ልል) ሴራ
> - ባለ ጥብቅ ሴራ
> - ባለ ጥምር ሴራ

- ባለ ነጠላ ሴራ (2009፤41)

### 2.2.5.1.ልቅ (ልል) ሴራ

ልል ሴራ ማለት ብዙም ጥብቅ ያለሆነ እና ያልጠነከረ ቀለል ያለ የሴራ አይነት ነው።

ፋታሁን እንግዳ ‹‹የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ›› በሚለው መፀሀፍ ስለ ሴራ በዚህ መልኩ አስፍሯል።

> በዚህ አይነቱ ሴራ የተገነቡ ተውኔት ታሪኮቹ ከቅንጣት ታሪኮቹ ትዕይንቶቹ ከትዕይንቶቹ ገቢሮቹ ከገቢሮቹ ጋር ያላቸው ቁርኝት እጅግ በላላ እና እንደ መነመነች ክር ሊበጠስ በቃጣው አይነት ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው። በባለ ልቅ ሴራ ተውኔት ውስጥ የሳቢያ እና የውጤት እርምጃዎች አሳማኝ እንዲሆኑ አይጠበቅባቸውም። (2009፤41)

በዚህ የሴራ አይነት የምክንያት እና ውጤት ትስስሩ በጣም ያሳሳ ነው። እንደዚህ አይነት ሴራዎች በአብዛኛው በቧልታይ ተውኔቶች እና በፊልሞች ላይ ነው የሚስተዋለው።

### 2.2.5.2. ጥብቅ ሴራ

ጥብቅ ሴራ ከልል ሴራ በተቃራኒው ወገን የሚቀመጥ የሴራ አይነት ነው። በጥብቅ ሴራ ግዜ በፊልሙ ወይም በፅሁፍ ውስጥ የሚገኙት እያንዳንዳቸው ጥቃቅን ሁኔቶች እና ታሪኮች በአንድ እየተገመዱ በመጨረሻ ወደ አንድ ሀሳብ የሚያመሩ ይሆናሉ።

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ›› በሚለው መፀሀፍ ስለ ጥብጥ ሴራ እንደሚከተለው አስፍሯል።

> በጥብቅ ሴራ ተውኔት ቁርጥራጭ ታሪኮች እርስ በእርሳቸውእንደ ድርና ማግ እየተሸራረቡ እና የተጣበቁ ሲሆኑ በስተመጨረሻ ወደ መደምደሚያ የሚያመሩ ናቸው።ይህም ማለት በስተ መጀመሪያው የተመሰረቱት ግጭቶች ሁሉ በመጨረሻ አመክኖ አዊነትን በጠበቀ መልኩ ይቀጥላል።
>
> (2009፤41)

በጥብቅ ሴራ ግዜ በዋናው ታሪክ ውስጥ ያሉ ትናንሽ ድርጊቶች፣ታሪኮች፣ግጭቶች፣ታሪኩ እየተገባደደ ሲሄድ እነሱም እየጠበቡ እየጠበቡ መጥተው በመጨረሻ ከዋናው ታሪክ ጋር በአንድ መደምደምያ ይጠቃለላሉ።

## 2.2.5.3. ጥምር ሴራ

ጥምር ሴራ ማለት በአንድ ድርሰት ውስጥ (ፊልም) ከአንድ በላይ የሆነ ሴራዎችን አጣምሮ የሚይዝ የሴራ አይነት ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ የተለያዩ ሴራዎች አንዱን ሴራ ከሌላው ሴራ ጋር የሚያዛምዳቸው ሁኔታ ይሆናል፡፡

ፋንታሁን እንግዳ ‹‹የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ›› በሚለው መፀሀፍ ስለ ጥምር ሴራ እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ይህ የሴራ አይነት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው የተለያዩ አላማዎችና ግቦች የያዙ ግን ደሞ እርስ በእርሳቸው ቤተሰባዊ ዝምድና ያላቸው ሴራዎችን በአንድነት ይዞ እናገኘዋለን ፡፡ ጥምር ሴራ ይሉት ተውኔት ቢፃፍ ለምሳሌ ከሁለቱ አንደኛው የሚባው ሴራም ሆነ ንዑስ ሴራው በየበኩላቸው ብዙ የተለያዩ ቁርጥራጭ ታሪኮች ሊኖራው ቢችሉ ም በመጨረሻ ሁሉም ጭፍጫፊ ሴራዎች የአብይ ሴራው አካል በመሆን እልባት ይፈልግላቸዋል፡፡ (2009፣41-42)

ጭምር ሴራ በባህሪው አብይ ሴራን እና ንዑስ ሴራን በአንድ ላይ አጣምሮ የሚይዝ የሴራ አይነት ነው፡፡ በዚህ ሴራ የተፃፈ ተውኔት በውስጡ የተለያዩ ሴራዎችን ይይዛል፡፡ ነገር ግን ታሪኩ እየተጠቃለለ ሲሄድ እነዛ የተለያዩ ሴራዎች እየተዛመዱ

## 2.2.5.4. ነጠላ ሴራ

ነጠላ ሴራ ከጥምር ሴራ በተቃራኒ ነው አንድ ዋና ታሪክ ወይም ግጭት ብቻ ይኖረዋል፡፡ ከዛ ታሪክ የወጣ ምንም አይነት ታሪክ ወይም ግጭት አይኖረውም፡፡

ሁሉም ጥቃቅን ታሪክ ዋናውን ከታሪክ የሚደግፍ እና ከዋናው ተሪክ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡

ፈንታሁን እንግዳ ‹‹የተውኔት አጻጻፍ ዘዴ›› በተሰኘው መጽሀፍ ስለ ነጠላ ሰራ ከዚህ በታች አስፍሮታል፡፡

> ነጠላ ሴራ የምንለው በመሰረቱ የልቅ ሴራ ወይም የጭብጥ ሴራ አይነት ሊሆን ይችላል፡፡ ከልቅ ወይም ከጥብቅ የሴራ አይ ነቶች የሚለየው ነገር ግን የተውኔቱ ታሪክና ድርጊት ሁሉ

አንድነቱን የጠበቀ ሆኖ ከመገኘቱ ላይ ነው፡፡ ከምንም አይነት

ከያዘውና ከሚያጠነጥነው ግጭት በመውጣት ተጨማሪ ግጭት

እና ታሪክ በመፍጠር በዋናው ሴራ መካከል ጠልቃ አያስገባምም፡

(2009፣42)

ይሄ የሴራ አይነት አንድ ነጠላ ታሪክ ወይም ነጠላ ግጭት ብቻ ይዞ እስከ ታሪኩ መጨረሻ ድረስ የሚጓዝ የሴራ አይነት ነው፡፡

## 2.2.6 ጭብጥ

ጭብጥ ማለት የፊልሙ የድርሰት ዋና (መሰረታዊ) ሀሳብ ሊያስተላልፈው የፈለገው ዋና መልዕክት ሲሆን አንድ የፊልም ጽሁፍ ወይም ድርሰት ከአንድ በላይ ጭብጥ ሊኖረው ይችላል፡፡ ነገር ግን እንደመነሻ ሀሳብ የሆነው ነገር ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና ሀሳብ ሊኖር ይገባል፡፡ ጭብጥ በአብዛኛው ተመልካቹ ወይም ደራሲው ጉዳዩ ብሎ የሚመለከተው ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እሱን የሚመለከተው ሲሆን ነው፡፡ የፊልም ጽሁፍ መአከላዊ ሀሳብ የጽሁፍ ይዘት ነው ማለት ይቻላል፡፡

የሻው ተሰማ ‹‹ስነ-ተውኔት ግለ መማሪያ›› በሚለው መጽሀፍ ስለ ጭብጥ እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

ጭብጥ የሚለው ፅንስ ሀሳብ ከተለያዩ ሌሎች ፅንሰ ሀሳቦች ጋር የመመሳሰል

ባህሪ አለው፡፡ ይዘት፣ ርዕሰ ጉዳይ፣መልዕክት የመሳሰሉት ከጭብጥ ጋር በጣም

ይመሳሰላሉ ሆኖም ጭብጥ ከነዚህ ሁሉ ለየት እንደሚል መገንዘብ አለብን፡፡ይዘ

ት አንድ ስራ በስራቱ(በአወቃቀሩ)ጠቅላላ አጠናቆ የያዘ ሽፋን ነው፡፡(2013፣201)

ጨብጥ ማለት የአንድ ድርሰት (ፊልም) ዋና ሀሳብ ሊያስተላልፈው የፈለገው ዋናው መልዕክት ማለት ነው፡፡

### 2.2.6.1 አካባቢያዊ ጭብጥ

አካባቢያዊ ጭብጥ በአንድ አካባቢ ብቻ የተወሰነ እውቀት ያለው ወይም ደግሞ ጭብጡ የአንድ ሰሞን ወቅታዊ ነገር የነበር ከዛ በኋላ የሚረሳ ወይም በሰው ጭንቅላት ውስጥ የማይታወስ ጊዜ የሚሽረው የጭብጥ አይነት ነው፡፡

ዘሪሁን አስፋው የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን ከሚለው መጽሀፍ ስለአከባቢያዊ ጭብጥ እደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> አንዳንድ ደራሲያን ዘላቂነት እና ሁለንተናዊነት በሌላቸው ጭብጦች ላይ ያተኩራሉ፡፡እንዲህ ያሉት ጭብጦች ደራሲ በአንድ ወቅት በአንድ የተወሰነ አካባቢ ብቻ የተፈጸመን ጉዳይ ለማንጸባረቅ የሚያመጣቸው እውነታነታቸው ለወቅቱ እና ለቦታው ብቻ የሆኑ የጭብጥ አይነቶች ናቸው፡፡(1995፣186)

አካባቢያዊ ጭብጥ ተጠቅመው የሚጻፍ ሰዎች ስራው የሚታወስ አይሆንም፡፡ እንደዚሁም ሁሉንም ሰው ያማከለ፤ሀሳቡን ሁሉም ሰው በቀላሉ መረዳት አይችልም፡፡

### 2.2.6.2. አለም አቀፋዊ ጭብጥ

አለም አቀፋዊ ጭብጥ ጽሁፉ (ስክሪፕቱ) የተጻፈበት ሀሳብ ለአንድ አካባቢ ብቻ ታስቦ ያልሆነ፤ በየትኛውም ቦታ ያለ ሰው ሊረዳው የሚችል እና ሊያግባባ በሚችል ሀሳብ መነሻነት ሲሰራ አለማቀፋዊ የጭብጥ ይዘት ይኖረዋል፡፡

ዘሪሁን አስፋው የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን በሚለው መጽሀፍ ስለ አለማቀፋዊ ጭብጥ ከዚህ በታች አስፍሯል፡፡

> አንድ ልብ - ወለድ  አብይ ጭብጥ የሰዎችን የጋራ ባህሪያት እና የጋራ ገጠመኞችን ያሳየ እደሆነ  ሁለንተናዊነት አለው ይባላል ፡፡ ሁለንተና ዊነት ካለው ደግሞ የተለያዩ የሂወት ፈርጆችን በመዳሰስ በማንኛውም ዘመን እና በየትኛውም ቦታ በሰዎች ሂወት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ

ቁም ነገሮችን መያዝ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በፍቅር በክፋት ፣ በደግነት፣ ቅናት፣ በየዋህነት እና መሰሪነት ወዘተ... ዙርያ የሚያጠነጥን ቢሆን እነዚህ በየትም ቦታ ባሉ ሰዎች ዘንድ የሚታዩ የጋራ ባህርያት ወይም ገጠመኞች በመሆናቸው ሁለንተናዊነቱ ግልጽ ይሆናል፡፡ (1995፣186)

አለማቀፋዊ (ሁለንተናዊ) ጭብጥ በየትኛውም አለም በየትኛውም ቦታና ጊዜ ያለ ሰው ጋር መድረስ እና ተቀባይነትን ማግኘት ይችላል፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ወይም በሌላ የቴአትር ጥበባዊ ትምህርትን ከሚሰጡ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ከተሰሩ ጥናታዊ ፅሁፎች ጋዜጣ በተወሰነ መልኩ ተዛማጅነት ወይም ተቀራራቢነት ያላቸው ፅሁፎች አሉ ፡፡ከነዛም መካከል አጥኚው ለዳሰሳ የመረጣቸውም

1 በሄለን ገብረመድህን በ1998ዓ.ም በአዲስአበባ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል "ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ" ማሚያነት የቀረበ ጥናታዊ ሲሆን "ሄርሜላ ፊልም ከፊልም አላባውያን አንፃር" የሄለን ነብረመድህንን ጥናትና ይሄን ጥናት የሚያመሳስላቸውና የሚያለያያቸውን ነጥቦች አሉ ፡፡ ይሄ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው ፡፡

በምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዳር ፣ የጥናቱ ዓላማ ፣ የጥናቱ ንዑስ ዓላማ ፣ የጥናቱ ዋና ዓላማ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ፣ የጥናቱ አወቃቀር ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦችን ይይዛል ፡፡

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት ፣ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ፣ ስለ ፊልም ፅሑፍ አላባውያን ፣ ስለ እውናዊ መቼት ፣ ስለ ሰዉ ሰራሽ መቼት ፣ ስለ ገፀባህሪ ፣ስለ ወጥ ገፀባሕርያት ፣ ስለ አስተኔ ገፀባህሪያት ፣ ስለ ግጭት ፣ስለ ቃለ ፊልም ፣ ስለ ሴራ ፣ ስለ ልል ሴራ ፣ ስለ ጥብቅ ሴራ ፣ ስለ ጥምር ሴራ ፣ ስለ ነጠላ ሴራ ፣ ስለ ጭብጥ ፤ እነዚህን ያካትትል፡፡

በምዕራፍ ሶስት ደግሞ ተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ታሪክ በአጭሩ ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ቃለ ፊልም ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ገፀባሕርያት ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ግጭት ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ሴራ ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ መቼት ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ጭብጥን ይመለከታል።

በአራት ደግሞ ማጠቃለያ ፣ የመፍትሔ ሀሳቦች ፣ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ፣ ዋቢ መፅሐፍትና አባሪን ያካትታል ።

የሄለን ገብረመድህን "ሄርሜላ ፊልም ከፊልም አላባውያን አንፃር" በሚል እርስ በተሰራው ጥናት ደሞ በሶስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው ።

በመጀመሪያው ክፍል መግቢያ ፣ የጥናቱ ዓላማ ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ አስፈላጊነትን ይይዛል።

በምዕራፍ አንድ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ፣ የፊልም ጥበብ ታሪካዊ ዳራ ፣ የፊልም ጥበብ አጀማመርና እድገት በኢትዮጵያ ፣ የፊልም ጥበብ በዘመነ ደርግ ፣ የፊልም ጥበብ በዘመነ ኢህአዴግ እነዚህን ያካትታል ።

በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የሄርሜላ ፊልም ታሪክ በአጭሩ ፣ የሄርሜላ የገፀባህሪያት አሳሳል ፣ የሄርሜላ ቪዲዮ ፊልም መቼት አቀራረብ ፣ የሄርሜላ ቪዲዮ ፊልም ከጭብጥ አንፃር አካቷል።

በምዕራፍ ሶስት የሄርሜላ ፊልም ከቴክኒክ አንፃር ፣ የሄርሜላ ቪዲዮ ፊልም ከትወና ከትወና አንፃር ፣ የሄርሜላ ቪዲዮ ፊልም ምስል ቀረፃ ፣ የሄርሜላ ቪዲዮ ፊልም ከመብራት አጠቃቀም አንፃር ፣ የሄርሜላ ቪዲዮ ፊልም ከድምፅ ግብአት አጠቃቀም አንፃር ፣ ማጠቃለያ ፣ ዋቢ መፅሐፍትን እነዚህን ይይዛል ።

የሄለን ገብረመድህን "ሄርሜላ ፊልም ከፊልም አላባውያን አንፃር" የተሰራው ጥናታዊ ፅሁፍ ከዚህ ፅሁፍ ጋር ያላቸው ልዩነት ይሄ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን የሄለን ገብረመድህን ጥናታዊ ፅሁፍ ደግሞ በሶስት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን በጥናታዊ ፅሁፏ ውስጥ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዓላማ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት የሚሉት እርሶች በምዕራፍ አንድ ሳይሆን በቅድመ ምዕራፉ ውስጥ ነው የተካተቱት ። ሌላው ልዩነታቸው ደግሞ ይሄ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ አላባውያን ሲሆን በሄለን ገብረመድህን የተሰራው ጥናት ደግሞ ሄርሜላ ፊልምን ከፊልም አላባውያን አንፃር ይመለከታል ።

የሚያመሳስላቸው ወይም የሚያዛምዳቸው ሁለቱም በአላባውያን ላይ መሰራታቸው ነው ። ሌላ የሚያመሳስላቸው ነገር ሁለቱም የፊልም ፅሁፍ አላባውያንን በተወሰነ መልኩ ያሳየናል(የሄለን ገብረመድህን ጥናት) የፊልም ፅሁፍ አላባውያንን በምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት በሚለው ንዑስ እርስ ውስጥ በሰፊው ይገለጻል ። ይህ የሚያመሳስላቸው ነጥብ ነው።

2. በወርቅነሽ ሽዋፈራሁ በ2012 ዓ.ም በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለ"ባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ" ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን "አትፍረድ ፊልምን ከዝግጅት ቴክኒክ አንፃር" ይመለከታል ። ይህም በጥናት አጥኚው ከሚያጠናው ከዚህ ጥናት ጋር የሚያዛምዱትና የሚለያዩት ነጥቦች አሉ ። አጥኚው የሚያጠናው ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ምዕራፍ የተከፋፈለ ነው።

በምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዳር ፣ የጥናቱ ዓላማ ፣ የጥናቱ ንዑስ ዓላማ ፣ የጥናቱ ዋና ዓላማ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ፣ የጥናቱ አወቃቀር ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦችን ይይዛል ።

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት ፣ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ፣ የፊልም ፅሁፍ አላባውያን ፣ እውናዊ መቼት ፣ ሰው ሰራሽ መቼት ፣ ገፀባህሪ ፣ ወጥ ገፀባህሪ ፣ አስተኔ ገፀባህሪ ፣ ግጭት ፣ ቃለ ፊልም ፣ ሴራ ፣ ልል ሴራ ፣ ጥብቅ ሴራ ፣ ጥምር ሴራ ፣ ነጠላ ሴራ ፣ ጭብጥ እነዚህን ያካትታል ። በምዕራፍ ሶስት ደግሞ የተፈጣሪ ፊልም ጭምቅ ታሪክ ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ቃለ ፊልም ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ገፀባሕርያት ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ግጭት ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ሴራ ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ መቼት ፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ጭብጥን ይይዛል ። በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ፣ የመፍትሔ ሀሳቦች ፣ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ፣ ዋቢ መፅሐፍትና አባሪን ያካትታል ።

የወርቅነሽ ሽዋፈራሁ ጥናት ደግሞ በምዕራፍ አንድ መግቢያ የጥናቱ ዳራ ፣ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ፣ የጥናቱ ዓላማ ፣ የጥናቱ ዓብይ ዓላማ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎች ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ፣ የጥናቱ አወቃቀር እነዚህን ያካትታል ።

በምዕራፍ ሁለት የንድፈ ሀሳብ ቅኝት ፣ የፊልም ምንነት ፣ ካሜራ ፣ የካሜራ ቀረፃ ፣ የካሜራ እንቅስቃሴ ፣ መብራት ፣ ትወና ፣ ምስል ቅንብር ፣ ግብአት ድምጽ ፣ ገፅቅብ ፣ ግጭት ፣ አልባሳት ፣ መቼት ፣ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ይይዛል ::

በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና የአትፍረድ ፊልም ታሪክ ፣ አትፍረድ ፊልም ከካሜራ አንፃር ፣ አትፍረድ ፊልም ከመብራት አንፃር ፣ አትፍረድ ፊልም ከፊልም ቅንብር አንፃር ፣ አትፍረድ ፊልም ከግብአተ ድምጽ አንፃር ፣ የአትፍረድ ፊልም ከገፅ ቅብ አንፃር ፣ አትፍረድ ፊልም ከመቼት አንፃር ፣ አትፍረድ ፊልም ከትወና አንፃር ፣ አትፍረድ ፊልም ከአልባሳት አንፃር ፣ አትፍረድ ፊልም ከጭብጥ አንፃር ፣ አትፍረድ ፊልም ከግጭት አንፃርን ይይዛል ::

በምዕራፍ አራት ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች ፣ አባሪና ዋቢ መፅሐፍትን ይይዛል ::ይህ የወርቅነሽ ሽዋፈራው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሣሥላቸውና  የሚለያዩት ነጥቦች አሉ: ይህን ጥናት የተፈጠረ ፊልም ጽሁፍን ከፊልም አላባውያን አንፃር ሲተነትን የወርቅነሽ ሽዋፈራሁ ጥናት ደግሞ አትፍረድ ፊልምን ከዝግጅት ቴክኒክ አንጻር ይመለከታል:: ሌላው ይህ ጥናት  በምእራፍ ሀለት ሥለ ፊልም አላባውያን ሠፋ ባለ መልኩ ሲያትት የወርቅነሽ ጥናት ደግሞ ሥለ ፊልም ዝግጅት መንነት ያብራራል:: እንዲሁም ሥለ ካሜራ ቅንብር  ግብአተ ድምጽ : መብራት:እንቅሥቃሤ ትወናን በዛው ምእራፍ በጽሁፍ የቀረበ ይህ ጥናት ደግሞ ከእልታ (በምስል )የምታዩ ነገሮች ላይ ትኩረት አያደርግም በፅሁፍ የቀረበው ድርሰት ነው የምተነተን ነው ::

የወርቅነሽ ሽዋፈራው እና ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ የምያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች በአራት ምዕራፍ የተዋቀሩ ናቸው :: ሌላው የምያመሳስላቸው አጥኚው በዝህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ በምዕራፍ ሁለቱ የፍልም ፅሁፍ አላባዊያን ብሎ የዘረዘራቸው አላባዎች በወርቅነሽ ሽፈራው ጥናት ውስጥ በምዕራፍ ሁለት የፍልም ዝግጅት አላባውያን በሚለው ንሁን ርዕስ ውስጥ ተነስቷል ::

3. ወለላ አበጀ 1998 ዓ.ም ወልቂጤ ዩንቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለ ባችለር ኦፍ አርትስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን "የነገን አልወልድም ፊልም ዝግጅት ትንተና " ይመለከታል ይህ ጥናት አጥኚው ከሰራው ከዝህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት እና ልዩነቶች አሉት ::

አጥኚው የሰራው ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ አራት ምዕራፎች ሲኖሩት በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥና ዳራ፣ የጥና አላማ፣ የጥናቱ ንዑስ አላማ፣ የጥናቱ ዋና አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ፣ የጥናቱ አወቃቀር፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች፣ የመፍትሔ ሀሳቦችን ይይዛል፡፡

በምዕራፍ ሁለት የተዛማች ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት፣ ንደፈ ሀሳባዊ ቅኝት፣ የፊልም ፅሁፍ አለባውያን፣ እውናዊ መቼት፣ሰው ሰራሽ መቼት፣ ገፀ-ባህሪ፣ ወጥ ገፀ-ባህሪ፣ አስተኔ ገፀ-ባህሪ፣ ግጭት፣ ቃለ ፊልም፣ ሴራ፣ ልል ሴራ፣ጥብቅ ሴራ፣ ነጠላ ሴራ፣ ጭብጥ እነዚህን ያካትታል፡፡

በምዕራፍ ሶስት ደግሞ የተፈጣሪ ፊልም ጭምቅ ታሪክ፣ የፊልሙ ቃለ ፊልም፣ የተፈጣሪ ፊልም ፅሁፍ ገፀ-ባህሪያት፣ የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ግጭት፣ የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ሴራ፣ የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ መቼት፣ የተፈጣሪ ፊልም ጭብጥን ይመለከታል፡፡

በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ፣ የመፍትሔ ሀሳቦች፣ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው፣ ዋቢ መጽሀፍትና አባሪን ይመለከታል፡፡

የወለላ አበጀ ጥናዊ ጽሁፍ በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ አብይ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ፣መፍትሄዎች እና የጥናቱ አወቃቀር፡፡

በምዕራፍ ሁለት የንድፍ ሀሳብ ቅኝትና የተዛማች ጽሁፎች ቅኝት፣ የንድፍ ሀሳብ ቅኝት፣ ፊልም ምንድ ነው፣ የፊልም ድርሰት አላባውያን፣ የፊልም ታሪክ፣ የፊልም ጭብጥ፣ የፊልም ገጸ-ባህሪ፣ የፊልም መቼት፣ የፊልም ሴራ፣ የፊልም ቴክኒክ አላባውያን፣ ካሜራ፣ የካሜራ ርቀት፣ የቅርብ ቀረፃ፣ ዝቅተኛ ማዕዘን፣ መብራት ፣ አልባሳት፣ ግብአተ ድምጽ፣ ገፅ ቅብ፣ የተዛማጅ ቅኝት ስራዎችን ይይዛል፡፡

በምዕራፍ ሶስት፣ የነገን አልወልድም ፊልም ጭምቅ ታሪክ፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከመቼት አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከጭብጥ አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከሴራ አወቃቀር አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ገፀ-ባህሪያት፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከጭብጥ አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከቴክኒክ አላባውያን አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከካሜራ አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከሩቅ ቀረፃ አንፃር፣ የነገን አልወድም ፊልም ከመካከለኛ ቀረጻ አንጻር፣ የነገን አልወድም ከቅርብ ቀረፃ አንፃረ፣ የነገን አልወድም ፊልም ከከፍተኛ ማዕዘን አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ዝቅተኛ ማዕዘን አንፃር፣ የነገን

አልወልድም ፊልም ከመብራት አጠቃቀም አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከአልባሳት አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከገፀ ቅብ አጠቃቀም አንፃር፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከቅንብር አንፃርን ይይዛል፡፡

በምዕራፍ አራት፣ማጠቃለያ፣የመፍትሄ ሀሳቦች እና ዋቢ መፀሀፍትን ይመለከታል፡፡

የወለላ አበጀ ጥናታዊ ፅሁፍ እና የአጥኝውን ጥናት የሚያለያያቸው የወለላ አበጀ ጥናት የነገን አልወልድም ፊልምን ዝግጅት መተንተን ሲሆን አጥኝው የሚሰራው ይህ ጥናት ደሞ የተፈጣሪ ፊልምን ጽሁፍ ከፊልም ጽሁፍ አላባውያንን አንፃር ይተነትናል፡፡

የወለላ አበጀ ጥናት በምዕራፍ ሁለት የፊልም ቴክኒክ አላባዊያንን ያብራራል፡፡ ካሜራ፣ የካሜራ ርቀት፣ አልባሳት... ይህ ጥናት ደሞ በምዕራፍ ሁለት ክፍሉ የፊልም ጽሁፍ አላባውያንን ያብራራል፡፡ የወለላ አበጀ ጥናት በምዕራፍ ሶስት፣ የነገን አልወልድም ፊልም ከዝግጅት ቴክኒክ አንጻር ሲዳስስ፣ ይሄ ጥናት ደሞ በምዕራፍ ሶስት የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍን ከፊልም ጽሁፍ አላባውያን አንፃር ይተነትናል፡፡

የሁለቱ ጥናቶች ተመሳሳይነት፣ ሁለቱም በአራት ምዕራፎች ነው የተዋቀሩት፡፡ የወለላ አበጀ ጥናታዊ ፅሁፍ በምዕራፍ ሁለት የንድፈ ሀሳብ ቅኝቱ ላይ ስለ ፊልም ድርሰት አላባውያን በዝርዝር አስፍሯል፡፡ በተመሳሳይ አጥኝው በምዕራፍ ሁለት ስለ ፊልም ጽሁፍ አላባውያን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ጭምቅ ታሪክ

‹የተፈጣሪዝም› ተፈጣሪዝም ከናቹራሊዝም የቴአትር ዘውግ የሚመደብ አዲስ ፍልስፍና ነው፡፡ ይህ ፍልስፍና መሰረት የሚያደርገው በድርሰት ላይ ነው፡፡ በዚህ በተፈጣሪዝም አጻጻፍ ሂደት ሁለት አይነት ደራሲዎች አሉ አንዱ በምዕናብ የተሳለን ታሪክ ከመጀመርያ እስከ ፍጻሜ ድረስ ያለውን የሚያስቀምጥ ሲሆን ሁለተኛው ግን ድርሰቱን ከጻፈ በኋላ በእውነተኛው አለም፣ የጻፈውን (የፈጠረውን በደንብ የሚመስልለትን በመልክ፣ በኑሮ፣ በአጠቃላይ የሰራውን ገጸ-ባህሪ ራሱን የሚመስልለትን (የሆነውን) ሰው ፈልጎ ታሪኩን እንደ አዲስ ከእውነታው ጋር እያመሳከረ መጻፍ ነው፡፡ የዚህ ፍልስፍና ባለቤት የቴአትር ጥበባት የአንደኛ አመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የሆነችው ገነት ናት፡፡ ገነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ለተመራቂ ተማሪዎች በተገባኘነት ጥናትዋን ታቀርባለች በዛ ሰዓት ልቡ በጣም የተነካ አብርሀም የተባለ ተማሪ በገነት ፍልስፍና በእጅጉ ተማርኮ፡፡ የገነትን ፍልስፍና ከራሱ ሂወት ጋር አብሮ እንደሚሄድ በማሰብ ተስማሙ፡፡ አብርሀም በሳለፈው ሂወት ፍትህ የተጓደለበት እና እጅግ የተበደለ ሰው ነው፡፡ ይሄ የተፈጣሪዝም ፍልስፈና ፍትህ እንደሚያስገኘው በማመን ገነትን በግል ያናግራታል፡፡ በሀሳብ ይግባባሉ፡፡ አብርሀም ገና በለጋነቱ የምታሳድገው እህቱ በሁለት ሴት ጓደኞቿ ሴራ በአምስት ወንዶች የመደፈር ጥቃት ደርሶባት አይኑ እያየ ሂወቷ ያልፋል፡፡ አብርሀም ወደ ጎዳና ወጥቶ ሂወቱን በአሳዛኝ ሁኔታ እየመራ አደገ የእህቱም ገዳዮች ፍትሀዊ ባልሆነ መልኩ ከፍርድ ቤት በነጻ ተሰናበቱ፡፡ የፍርድ ቤቱም ዋና ዳኛ የገነት አባት ነበሩ፡፡ አንደኛው ወንጀለኛ ጓደኛቸው ስለነበር በነጻ ሊለቁት ችለዋል፡፡ እናም ከአመታት በኋላ አብርም በገነት አዛዥነት ‹‹በተፈጣሪዝም›› አጻጻፍ ስልት የሚጽፋቸው ፊልሞች በሰዎች ዘንድ እጅግ ተወዳጅነትን አተረፉ በተፈጣሪዝም አጻጻፍ ዘዴ መሰረት በሂወቱ የዘጋውን ደሴዎች እየከፈተ ታሪኩን ማስቀጠል ይጀምራል፡፡ የእህቱን ገዳዮች አስገዳዮች አንድ በአንድ የተለያየ መንገድ እየተጠቀመ ከፊታቸው ሞትን ይደቅንባቸው ጀመረ፡፡ ይገባቸዋል ብሎ ያሰበውን የሞት ቅጣት እየቀጣቸው ታሪኩን መጻፍ ቀጠለ በዚህም ምክንያት በተደጋጋሚ የክስ ፋይል እየተከፈተበት መጣ ነገር ግን የተፈጣሪዝም (የፍልስፍናው) ባለቤት ገነት የፖሊስ ወንጀል ክትትሉ አባል በመሆን ነገሮችን ታስተካክልለት ጀመር፡፡

ነገር ግን የወንጀል ቡድን መሪ በጣም ጠንካራ እና ሀቀኛ የሆነው ነብዩ በጣም ይፈትናት ነበር፡፡ ሆኖም ግን ወንጀለኛውን (ተጠርጣሪውን) ለመያዝ ከብዶታል ያዝኩት ሲል ያመልጠዋል በአካል አግኝቶ ቢያወራውም እንኳን ምንም አይነት ማስረጃ ሊያገኝበት ባለመቻሉ በጣም ዕልህ ይይዘዋል፡፡ እግር በእግር እየተከታተለ ማስረጃ ሊያገኝ መጣሩን ይቀጥልበታል፡፡ ይህ ሁኔታው ለአብርሀም ምቾት ስላልሰጠው የሚስቱን ስም በማንሳት እና እሱ እቤት በሌለበት ነብዩ እንደደወለላት አስመስሎ እቃ በመላክ ሚስቱ በእሱ እይታ ውስጥ እንደሆነች በማሳየት ሀሳቡን ለመስረቅ ሞክሯል፡፡ የፖሊስ ቡድኑ ባደረገው ያልቆመ ምርመራ የአብርሀም ፍልስፍና ከሚች እህቱ ፍትህ ማጣት ጋር የተያያዘ እደሆነ ይደርሱበታል፡፡ የሚች እህቱን የቆየ ፋይል በማውጣት የወንጀለኞቹን ስም እና አድራሻ በማየት በሂወት ለተቀሩት ጥበቃ ማድረግ ይጀምራሉ በዛም ሁሉ ጥበቃ ወንጀለኞቹ ሊያድኑአቸው አልቻሉም፡፡ በተለያየ ስልት ተጠቅሞ ወንጀለኞቹን በሞት መቅጣቱን ይቀጥላል፡፡ ይህ ሲሆን ለሚጠበቁት ወንጀለኞች ተገቢውን ጥበቃ ባለማድረግ ነብዩ  ከስራ ገበታው ይሰናበታል፡፡ ገነር ግን የዚህ የወንጀል ጉዳይ እና መረጃ ከውስጥ የመሹለኩ ጉዳይ በጣም  ስላሳሰበው ከውጭ ሆኖ ስራውን በግል ይቀጥላል በኋላም ወደ አብርሀም የቀድሞ ትምህርት ቤት (ዩኒቨርሲቲ) በመሄድ ስለተፈጣሪዝም ሲጠይቅ የዚህ ፍልስፍና ባለቤት ገነት መሆኗን ያውቃል፡፡ እየሰለለች እንደነበረም ይገባዋል፡፡ ይህንን ጉዳይ ከወንጀል ተከታታይ ቡድኑ እና ከአዛዦቸው ጋር በመነጋገር ወደ ስራ ገበታው ተመልሶ ለቀሩት ሁለት ወንጀለኞች ከለላ ለመስጠት ወደ ወንጀለኞቹ መኖሪያ ቤት ሲሄዱ ገነት ሰውየውን ገድላው ስትወጣ እጅ ከፍንጅ ይይዟታል፡፡ ወደ እስር ቤት ትገባለች፡፡ አብርሀም በድጋሚ ተይዞ ቢመረመርም ምንም አይነት የወንጀል ማስረጃ ሆነ መረጃ ማግኘት አልቻሉም፡፡ ገነትም ያ እህቱ በግፍ የተገደለችበት ህጻን እሷ እንደሆነች ለፖሊሶች አሳመነች አብርሀምም በነጻ ተለቀቀ፡፡ በተለቀቀ ቀን የቀረው የመጨረሻው የእህቱ ገዳይ በህክምና መርፌ  ብዙ ቦታ ተወጋግቶ ሞቶ ተገኘ እንደ ተለመደው አጠገቡ የወረቀት መርከብ ነበር፡፡ መርማሪ ነብዩ ለገነት የመርከቡን ምንነት ሲጠይቃት እንዲህ ብላ መለሰችለት የኖህ መርከብ መልካሙን ነገር ሁሉ ሰብስባ ህዝብን ከጥፋት ታድጋለች ክፉዎችም ጠፉ፡፡ አሁን ግን የምህረት ዘመን በመሆኑ፡፡ መልካሞቹን ትተን ክፉዎችን በራሳችን መርከብ ወደ ፈጣሪ እንሸኛቸዋለን አለችው፡፡

ነብዩ በኋላ ባደረገው ተጨማሪ ምርምር ሁሉንም እውነት ይደርስበታል የገነት አባትም ያንን ፍርድ ያዛባው፤የአብርሀምን እህት ገዳዮች በነጻ ያሰናበታቸው ዳኛ እሳቸው መሆናቸውን ለማወቅ ቻለ፡፡ ያንንም ለገነት ይነግራታል፡፡ አብርሀም የአባቷን ጥፋት በተዘዋዋሪ እሷ እንድትቀጣው ማድረጉን ይነግራታል አብርሀምም መሰወሩን ነገራት አብርሀም ቢሮው ላይ

ተገልብጦ የተቀመጠውን ሚዛን አስተካክሎ ያሰቀምጠዋል ‹‹ተፈጣሪዝም›› የሚለው ፊልም ተመርቆ ‹‹ፖስተሩ›› መበተን ጀመረ፡፡

## 3.1 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ትንተና ከፊልም ጸሁፍ (ስክሪፕት) አላባውያን አንጻር

### 3.1.1. የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ መቼት

ታሪኩ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው ጊዜው አሁን ያለንበት ዘመን እና በምልሰት ከሀያ አመት በፊት የነበረን የአብርሀምና የእህቱን አኗኗር፤ ረዳት የሌላቸው ድሆች እደነበሩ እና ኑሮአቸውም ጎዳና ላይ እንደነበረ ለማየት ያስችላል፡፡

ትዕይንት ሀያ አራት ገጽ 22

Flash back

ቀን መንደር ወስጥ

/ትንሹ ልጅ ብጥቅጣቂ ቲሸርት ለብሶ ዝናብ እየለበሰ ጥግ ላይ ቁጭ ብሎ እየተንቀጠቀጠ

ከዝናቡ ለማምለጥ የሚሮጡ ሰዎችን ያስተውላል/

የአብርሀም ኑሮ ጎዳና ላይ እደነበረና አስከፊ አኗኗር እደነበረው ያሳያል፡፡ ስክሪፕቱ (የፊልም ጽሁፉ) ላይ በምልሰት ወደ ኋላ ሲመልሱን የሚጠቀሙት የተለየ አልባሳት ወይም በድሮ ግዜ የነበረ የቤት ቁሳቁስ የለም፡፡ በዚህም ምክንያት ግዜውን በደንብ ለመግለጽ (ለማሳወቅ) አልቻለም፡፡ ነገር ግን ተውኔቱን አሁን ወዳለንበት ሲመልሱት የአሁኑ ግዜ እደሆነ የተለያዩ ነገሮች ያሳዩናል፡፡ ከነዛም መካከል አብርሀም ሰይፉ ፈንታሁን ሾው ላይ ቀርቦ እንመለከታን፡፡

ገጽ 48 ትዕይንትን 73

ቀን ሰይፉ ስቱዲዮ ውስጥ

አብርሀም ይስቃል ሰይፉ ፎቶ ከሚያስቀምጥበት ስር የጦር ጋሻ አንስቶ አሳየው ተመልክቶ ሳቀ

ሰይፉ

እኔምልህ በተደጋጋሚ ትከሰሳለህ በተደጋጋሚ ደግሞ ነጻ ትወጣለህ ይመስልኛል አሁን ባስመረከው ፊልም ምክንያት ታስረህ ነበር

/እጁን እያወራጨ/

የሆነ ለመናገር ትንሽ አስቸጋሪ ነው አይደል

አብርሀም

ምን አለ መሰለህ ሰይፍሻ አንዳንዴ እንዲ ዝነኛ በምትሆንበት ሰዓት ብዙ ነገር ሊገጥምህ ይችላል፡፡ እንደውም ከዚህ የከፋ ነገር

በሰይፉ ፈንታሁን ሾው አሁን ያለንበት ዘመን ላይ ድረስ እየተላለፈ የሚገኝ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሲሆን የቅርብ አመታት ቀርጻ መሆኑን የሚያረጋግጥልን ቃለ ምልልሶች አሉት፡፡

ገጽ 51 ትዕይት 75

አብርሀም

እም በርግጠኝነት መናገር ምፈልገው

/ወደ ካሜራው በትኩረት እያየ/

የአብርሀም ታሪክ ተጀመረ እንጂ አላለቀም

ሰይፉ

ለአርቲስት አብሀርም

/ሰይፉ እየታየ የመልካቹ ጭብጨባ ተሰማ/

ሰይፉ

እና ጋሻውን አውርደው ችግር የለም እያልከኝ ነው ነገሩስ አንፈራም ያው ልጆች አሉ ትዳርም እንጂ አንፈራም ጎበዝ!

የአሁን ጊዜ ትዕይት መሆኑን በዚ ቃለ ምልልስ ለማረጋገጥም ያስችላል፡፡ እንዲሁም በአሁን ሰዓት ያው የአብርሀም የ ‹‹ኢኮኖሚ›› ደረጃ ጥሩ የሚባል እንደሆነ ከሚያደርገው ቃለ ምልልስ ማወቅ ይቻላል ከአንድ በላይ የሆነ ፊልም ማስመረቁ፤ እና በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ማግኘቱ፡፡

### 3.1.1.1 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ከእውናዊ መቼት አንጻር

የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) አጠቃላይ መቼቱ እውናዊ መቼት ነው። ለዚህም ማሳያነት በገሀዱ ዓለም ያለውን እንቅስቃሴ፣ ተፈጥሮአዊ የቦታ ገጽታዎች፣ የቦታ አቀማመጦች በአካል የሚታወቅ እና የሚጨበጥ ነው።

ገጽ 1 ትዕይት 1

ቀን ብሄራዊ ትያትር መግቢያ በር ውጭ

አብርሀም ረዘም ሞላ ያለ ሰውነት አለው የቴአትር ቤት መግቢያ ጋር ቁጭ ብሎ መጽሀፍ ሲያነብ ይታያል የቴአትር ቤቱ በር ላይ ቆመ ይታያል።

የተጠቀሙት ቦታ በአካል የምናውቀው ነው። በአካል ባናውቀው እንኳን በአዕምሮአችን አንደዛ አይነት ቦታ ሊኖር እንደሚችል የሚያሳምን ነው። እንዲሁም በእዚህ ፊልም ጽሁፍ ገጸ ባህሪያቱ የሚለብሱት አለባበስ የፀጉር(እስታይል) አሰራር የታወቀ እና እውነት ባለው መልኩ የቀረበ ነው።

ገጽ 13 ትዕይንት 12

ቀን መመርመሪያ ክፍል ውስጥ

ገነት

ይቅርታ ኮማንደር!

/እነርሱ ወዳሉበት ተጠግታ። ወጣትና ቆንጆ ናት። ፀጉርዋን ወደ ኋላ አሲዛ ጥቁር ሙሉ ልብስ ለብሳለች።

በዚህ የፊልም ጽሀፍ ውስጥ ያሉት መቼቶች እውናዊና በገሀዱ አለም ያለውን የሰውን እንቅስቃሴ አስተዳደግ እንዲሁም ተፈጥሮአዊ አቀማመጡን የጠበቀ ነው።

የተፈጠረ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት)፣ የፊልም ጽሁፍ እንደመሆኑ መጠን ትዕይንቶቹ (መቼቱ) በፍጥነት ሲለዋወጡ እንመለከታለን። ነገር ግን ምንም እንኳን ቦታና ግዜዎቹ ቶሎ

ቶሎ ቢለዋወጡም ቦታዎቹ ብዙ እንግዳ የማይሆኑ እና የምናቃቸው መስሎ እንዲሰማን የሚያደርግ በመሆኑ ብዙም አይወሳሰብም፡፡

### *3.1.1.2* የተፈጣሪ ፊልም ጽጉፍ (እስክሪፕት) ከሰው ሰራሽ መቼት አንጻር

የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) የተጠቀመው መቼት እውናዊ መቼትን ብቻ ነው ፡፡

በፊልም ፅሁፉ ምንም አይነት ተፈጥሯዊ ያልሆኑ ፤ አዘጋጁ በራሱ ምናብ የፈጠራቸው የራሱ የመቼት አገላለፆች የሉትም ፡፡

## 3.1.2 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (እስክሪፕት) ከገፀባህሪያት አንፃር

የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ውስጥ ወጥ ገጸ-ባህሪያት ስንመለከት ታሪኩ በዋነኝነት ተሸክመው የሚሂዱት በዋናነት የምንጠቅሳቸው አስር ገፀ-ባህርያት ይገኙበታል፡፡ እነሱም አብርሀም፣ ገነት፣ ነብዩ፣ የአብርሀም እህት ርብቃ፣ ሮዛ(ሴተኛ አዳሪዋ) እና አምስት የአብርሀምን እህት (ርብቃን) የደፈሩዋት ወንዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ገጸ-ባህርያት ታሪኩ እየተንሰላሰለ እደሄድ ያስቻሉ ገጸ ባህርያት ናቸው፡፡ በዚ ፊልም ጽሁፍ ውስጥ አስተኔ ገጸ-ባህርያትም ይገኙበታል፡፡ የነሱ አለመኖር ታሪኩ ላይ ወሳኝ የሚባል ተጽዕኖ የማይፈጠሩ ገጸ-ባህርያት ናቸው፡፡ ታዲዮስ (መርማሪ)፣ ኮማንደር (የመርማሪዎቹ ሀላፊ)፣ሳሙኤል፣(መርማሪ)፣ፕሮፌሰር(የዩንቨርስቲ መምህርት)፣ የወንጀለኛው ልጅ እነዚህ በተውኔቱ ውስጥ የነበሩ አስተኔ ገጸ-ባህሪያት ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት አጥኝው ወጥ ገጸ-ባህርያትን በዚህ መልኩ ይተነትናቸዋል፡፡ የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክርፕት) የገጸ ባህርያት ገለጻው በጣም ያነሰ ነው፡፡ ስለ ሁለት ገጸ ባህርያት ብቻ አካላዊ ሁኔታ በትንሹ ይገልጻል፡፡

ገጽ 1 ትዕይንት 1

ቀን ብሔራዊ ቴአትር መግቢያ በር ውጭ

አብርሀም ረዘም እና ሞላ ያለ ሰውነት ያለው የቴአትር ቤት መግቢያው ጋር ቁጭ ብሎ መፅሀፍ ሲያነብ የታያ፡፡

ገጽ 13 ትዕይንት 12

ቀን መመርመሪያ መከታተያ ክፍል ውስጥ

ገነት

ይቅርታ ኮማንደር!

/እነሱ ወዳሉበት ተጠጋች፡፡ ወጣትና ቆንጆ ናት ፡፡ ጸጉሯን ወደኋለ አስይዛ ጥቁር ሙሉ ልብስ ለብሳለች/፡፡

የፊልም ፅሁፍ (ስክሪፐቱ) የገጸ ባህሪያቱን አካላዊ ገለጻ በዚህ መልኩ አስፍሯል ነገር ግን አጥኚው ገጸ ባህርያት ከገጸ-ባህርያት ጋር በሚያደርጉት ንግግር ስለ ገጸ-ባህርያት ተጨማሪ ገለጻ ለማወቅ ችሏል፤ አብርሀም ብቸኛ እንደሆነና እዳላገባ፣ አስተዳደጉም ጎዳና እንደሆነ፣ የሰውፍቅን ተጠምቶ እንዳደገ እና አይዞህ ባይ እንዳልነበረው ቃለ ምልልሳቸው ያሳየናል፡፡

ገጽ 23 ትዕይንት 24

ቀን ምርመራ ክፍል ወስጥ

ገነት

ልጅነትህን ተነጥቀሀል

/አብርሀም ቀና ብሎ አያት ፡፡ ገነት በሀዜነታ መሰል አይን አይኑን እያየች፡፡/

ገነት

ስትወድቅ የሚያባብልህ ሲከፍህም አይዞህ በርታ የሚልህ ማንም ከአጠገብህ የለም

Flash back

ትዕይት 26

ቀን ቆሻሻ መጣሮ አካባቢ ውጭ

ከአንድ ገንዳ ስር ቁጭ ብሎ እንባውን እየጠረገ በገንዳው ውስጥ ምግብ እየተሻሙ የሚበሉ የጎዳና ልጆችን ያስተውላል፡፡

Out of flash back

ትዕይንት 27 ገጽ 23

ቀን ምርመራ ክፍል ውስጥ

ገነት

ሲርብህ እንኳን ከቆሻሻ ገንዳ ወስጥ የሞተ አይጥ የተኛበት ፍርፍሬ ከቢጤዎችህ ጋር እየተሻማህ ትበላለህ

ከዚህ ቃለ ምልልስ ምን ያህል መራራ ሂወት እንዳሳለፈ ያሳየናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አብርሀም የተማረ እና በትያትር ጥበባት የመጀመርያ ድግሪ ያለው የፊልም ደራሲ ፀሀፊና አዘጋጅ ነው፡፡ በዛም ዝናን ያተረፈ እንዲሁም በስራው በሰዎች ዘንድ ተወዳጅነት ያተረፈ በሂወቱ ያጣውን ፍትህ በራሱ መንገድ ለማስፈን እቅድ አላማ ያለው ወጣት ነው፡፡

ገነት ወጣት እና ቆንጆ ስትሆን የተማረች በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የቴአትር ጥበባት የድግሪ ምሩቅ ነች እንዲሁም የሀብታም ልጅ ናት፣ ላመነችበት ነገር ፈጽሞ ወደኋላ የማትል አንድ ነገር አደርጋለሁ ብላ ካሰበች የማንም ሰው ክልከላ የማያስቆማት ሴት ነች፡፡

ገጽ 28 ትዕይት 33

ቀን ምርመራ ክፍል ውስጥ

አብርሀም

ለምሳሌ አንቺ

/ገነት ግር ተሰኝታ/

ገነት

እኔ?

አብርሀም

እሽም የሆነ የሀብታም ልጅ ትመስያለሽ

/ገነት ኮስተር ብላ አየችው/

ትዕይንት 34

ቀን ሰፊ ቢሮ ውስጥ

አንድ ሽማግሌ የልብስ ጨረቃ ጨርቅ ማምረቻ በመስኮት በኩል የምርት ሂደቱን ይመለከታል ገነት ስትገባ በፈገግታ ዞሮ ሲቀበላት ይታያል፡፡

ትዕይንት 35 ገጽ 28

ቀን ምርመራ ክፍል ውስጥ

አብርሀም በካቴና ተነባብረው በታሰሩት እጆቹ የግራ ጥፍሩን ጣት ቆሻሻ በሌላኛው ቀኝ እጅ ጣት እያወጣ፡፡

አብርሀም

እርግጠኛ ነኝ ይሄን ስራሽን ቤተሰቦችሽ አይደግፉትም አንቺ ግን አሻፈረኝ አልሽ፡፡

ትዕይት 36 ገጽ 29

ቀን ሰፊ ቢሮ ውስጥ

ሽማግሌውና ገነት ይጨቃጨቃሉ ገነት ተነስታ ጥላው ከቢሮ ወጣች

/ሽማግሌው አንገቱን ደፍቶ በማዘን ስሜት አንገቱን ይነቀንቃል/

ገነት በከፍተኛ የወንጀል መርማሪነት የምትሰራ፣ መሸነፍ የማትወድ፣ እራስዋ በፈጠረችው ፍልስፍና የምትኖር፡፡ የምትሰራውን ስራ የምትሰራው ወዳው ሳይሆን ለፍልስፍናዋ እንደ ማስፈጸሚያ ስለሚሆንላት ነው፡፡

ነብዩ አካላዊ አሳሳሉ ያልተገለጸ ሲሆን ባለትዳር ነው ትዳሩን (ባለቤቱን) አብዝቶ የሚወድ፤ በከፍተኛ የወንጀል ምርመራ ክፍል ውስጥ የምርመራው መሪ ሆኖ የሚሰራ መርማሪ ፖሊስ ነው፡፡ በጣም ቆፍጣና እና ለእውነት ለፍትህ የቆመ ስራውን የሂወቱ አካል ያደረገ ጎበዝ መርማሪ፣ የጀመረውን ሰራ ሳይጨርስ የማይተኛ እልኸኛ ነው፡፡ አላማውም የጀመረውን (የወንጀል) ምርመራ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ (በአሸናፊነት) አጠናቆ እርካታን ማግኘት ነው ፡፡ ነብዩ በሰራው ስህተት ምክንያት ከስራው ቢታገድም በግል ስራውን ለመቀጠል ወሰነ፡፡

ትዕይንት 168 ገጸ

ቀን ምርመራ ክፍል ውስጥ

ኮማንደር

አሁን ዝም ብለህ ባጁን አስረክበኝና ውጣ! አስረክበኝ ብዬሀለሁ

ነብዩ

/ባጁን መለሰ ገነትን አየት አድርጓት/

መልካም ዕድል

/ነብዩ ከቢሮው ወጣ/

ትዕይንት 177 ገጽ 131

ቀን ፕሮፌሰር ቢሮ ውስጥ

/አንዲት በእድሜ የጠኑ ፕሮፌሰር በቤሮአቸው ውስጥ ተቀምጠው ፍጹም ስሜታዊ በሆነ ስሜት ተውጠው መነጸራቸውን አውልቀው ጠረጴዛ ላይ ጣሉትና የነብዩን አይን እያዩ/

ፕሮፌሰር

Well አብርሀም

/ራሳቸውን አየነቀነቁ/

Such talented man ብዙዎች በዝናው ነው የሚያውቁት እኔ ግን አስቀድሜ ታላቅ እንደሚሆን አውቅ ነበር

ነብዩ

/በውስጡ እያላገጠ/

ታላቅ ብቻ ምንም ግምቱ የለሽም ፕሮፌሰር

ኸም! ከሁሉ ታድያ የሚያስገርመኝ የመመረቂያ ጸሁፍ ነበር by any chance ስለ ‹‹ኢዝምች›› ታውቃለህ

ነብዩ ከስራ ገበታው እንኳን ታግዶ የጀመረውን የወንጀል ምርመራ ባለማቋረጥ ለመስራት ወደ ኋላ የማይል ለፍትህ የቆመ ሀቀኛና እልከኛ ሰው ነው፡፡

ርብቃ የአብርሀም አህት ወጣት ናት እስክሪፕቱ ስለአካላዊ ሁኔታዋ የሚገልጸው ነገር የለም የቡና ቤት ሰራተኛ ናት እራስዋንና ታናሽ (ህጻን) ወንድሚን ለማኖር የምትደክም ሴት ናት።

የተቀሩት ርብቃን ደፍረው የገደሉዋት አምስት ጎረምሶች ናቸው። እነሱም ሰውነታቸው እንጂ አዕምሮአቸው ያልጠነከረ ለስሜታቸው ባርያ የሆኑ ጨካኝ ልባቸው የማይራራ ሰዎች ናቸው።

በአጠቃላይ በተፈጣሪ የፊልም ጽሁፍ ውስጥ ያሉት ገጸ-ባህርያት ታሪኩ እንደሚፈልገው ከታሪኩ ጋር አብሮ የሚሄድ ማንነት ያላቸው ታሪኩ ታአማኒነት እንዲኖረው አድርገውታል።

### 3.1.3 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ከግጭት አንጻር

በዚህ ፊልም ፅሁፍ (ስክሪፕት) ውስጥ የሚስተዋለው የግጭት አይነት ሁለት አይነት ነው አንደኛው ሰው ከሰው ጋር (person VS person) የምንለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሰው ከፈጣሪው ወይም ከእጣፈንታው ጋር (person VS GOD/fate) ናቸው።

#### *3.1.3.1 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ግጭት ሰው ከሰው ጋር*

የተፈጣሪ ፊልም ግጭት በአብዛኛው ሰው ከሰው ጋር የሚያደርገው ግጭት አይነት ይስተዋልበታል። የመጀመሪያው ሰው ከሰው ጋር ግጭት የጀመረው አብርሀም ከወንጀለኞቹ ጋር ነው፤ እህቱን በጭካኔ አይኑ እያየ አስገደደው ይደፍሯታል።

በዛም አብርሀም ለወንጀለኞቹ ከፍተኛ ጥላቻ እና የበቀል ስሜት አደረበት።

አብርሀም ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ በመሆን ድርሰቱን በመጻፉ የወንጀሉ የመጀመሪያ ተጠርጣሪ በመሆን የወንጀል መርማሪዎቹ ያስሩታል። ከመርማሪ ፖሊሶችም ጋር በንግግር ያለመግባባቶች (ግጭቶች) ይፈጠራሉ።

ገጽ 11 ትዕይንት 11

ቀን                መመርመሪያ ክፍል                ውስጥ

ነብዩ

ስማ ከአንተ አይነቱ አረመኔ ጋር ጊዜዬን ማጥፋት አልፈልግም እና

/አብርሀም በንቀት እጁን ወደ ላይ አንስቶ አስቀመው/

አብርሀም

አይ በእኔ አላም እኔ ያልኩት ብቻ ነው አረመኔም በለው ጨካኝ

ነብዩ

በእውነተኛው አለም ባክህ

አብርሀም

ምን ሶስት ሺህ ይሞላል ደሞዝህ?

/አብርሀም የለመጣ ሳቅ እየሳቀ/

ስትቆራረጥማ አይጣል ነው በአመት ሁለቴ አቺ … ከስክስ …ኽም!

አታፍርም እንዲ አሁን አንተም አለም አለህ?

/ፊቱን ወደ በሩ አዙሮ/

በኛስ አለም ይለኛል እንዴ …?

/ነብዩ ድንገት እልህና ንዴቱ ገንፍሎ አነቀው፡፡/

ነብዩ

አንተ ውሻ እገልሀለሁ!

አብርሀም ከነብዩ ጋር፤ አካሄዱ ስላስፈራው ሀሳቡን ለመበታተን ሚስቱ አካባቢ በማንዣበብ፣ እሱ የላከ አስመስሎ ስጦታ በመላክና ለነብዩም መልዕክት በመላክ ነብዩን ሲያስፈራራው፡፡

ነብዩ በሚሰራው የወንጀል ክትትል ስራ ከጥንቃቄ ጉድለት ወይም በግድ የለሽነት ስህተት ተፈጥሮ ወንጀለኛ ሞቷል በሚል ከኮማንደሩ ጋር ተጋጭቶ ከስራ ታግዷል፡፡

ገጽ 116 ትዕይት 168

ቀን ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ

/ኮማንደር ቢሮ ውስጥ ነብዩ እና ገነት ተቀምጠዋል ኮማንደር በጣም በተናደደ መልክ ገጽታ እየተመለከታቸው/

ኮማንደር

አንድ ተራ ወንጀለኛ ለመያዝ የንጹህ ሰው ህይወት አደጋ ውስጥ ትከታለህ ዛሬ የአንድ ዜጋ ህይወት አልፏል በአንተ እንዝላልነት ይገባሀል!

ነብዩ

ኮማንደር በሚገባ የሰው ሀይል አደራጅቼ ጉዳት ሊያስከትል በማይችል መልኩ ነበር ቡድኑን የመራሁት

ኮማንደር

ሲጀምር ማን ፍቃድ ሰጠህ አሳውቀሽኛል?

ነብዩ

ግን እኮ

ኮማንደር

ምንም ግን እኮ የለውም ነግሬህ ነበር አስታውስ ሚሸፍንልህ ማንም የለም አሁን በአንተ ጉዳይ ከበላይ እስክንወያይ ከስራ ታግደሀል ባጅህን አስረክበህ

ገነት ከስራ ባልደረቦችዋ ጋር ትጋጫለች የግጭቱም መንስኤ እዛ ቢሮ (መስሪያ ቤት) ውስጥ ስትሰራ በቆየችበት ሰዓት ሁሉ ሰላይ እንደነበረች እና ሲከታተሉዋቸው የነበሩት የግድያ ወንጀሎች ሁሉ በእሷ አማካኝነት የሚከናወኑ እንደሆኑ ይታወቅባታል፡፡

ገጽ 101 ትዕይት 190

ቀን ውጪ

ነብዩ

ቁሚ እተኩሳለሁ

/ወደ ላይ ተኮሰ ገነት ሩጫዋን አላቆመችም ነብዩ ተሯሩጦ እላይዋ ላይ ዘሎ ወደቀባትና ተንከባለው ወደቁ ነብዩ ሽጉጡ ተሽቀናጥሮ ራቀው ገነት ከወደቀችበት ተነስታ ከበድ ያለ

ድንጋይ እንደተኛ ወረወረችበት እንደምንም ሸውዷት መሳሪያውን ለማንሳት ሲጣጣር ገነት ሌላ ድንጋይ አንስታ እጇዋን ስትሰቅል ነብዩ ሽጉጡን አንስቶ ጀገረባት።/

ነብዩ

እኔ አንቺን ብሆን ይኼን አላደርግም

ገነት በእስር ቤት እንዳለች አባትዋ ዳኛ እንደነበሩ፤ የአብርሀምን እህት ጉዳይ እሳቸው ይዘውት እንደነበርና ፍትህ እንዳዛቡ ሰማች አብርሀምም በአባትዋ ጥፋት እሷ እንድትቀጣ ይህን እንደአደረገባት ተነገራት። በዚያም ምክንያት በአብርሀም በጣም ትበሳጫለች።

## 3.1.3.2. የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ግጭት ሰው ከፈጣሪ ወይም ከእጣፈንታ ጋር

በዚ የፊልም ጽሁፍ (ስክሪኘት ) ውስጥ ሰው ከፈጣሪ ወይም ከእጣፈንታው ጋር ሲጣላ እንመለከታን። የተፈጣሪዝም ፍልስፍና ባለቤት የሆነችው ገነት በራስዋ ፍቃድና ፍላጎት እዚህ ምድር ላይ ጻድቃን (ወንጀለኛ ያልሆኑ ሰዎች)ብቻ ነው መኖር ያለባቸው የሚል ሀሳብ በማራመድ የሰውን በሂወት የመኖርን ፍቃድ በራስዋ በመወሰን ከፈጣሪ የተጻረረ መንገድ ስትሂድ፣ ሰው ከፈጣሪ ጋር የሚባለውን ግጭት ትፈጥራለች።

ገጽ 149 ትዕይንት 144

ቀን ምርመራ ክፍል ውስጥ

ገነት

/ፈገግ ብላ/

በኖህ ዘመን ሶዶማውያን በፍትወተ ስጋ ተጠምደው አምላክን በከዱ ግዜ ኖህን መርከብ እዲሰራ አዘዘው

/የሰራችውን የወረቀት መርከብ በመሀላቸው አስቀምጣ/

/ሳቅ እየከጀላት/

እኔ አማኝ አይደለሁም ግን የዚህ ታሪክ የሆነ ነገሩ ልክ አይደለም

ነብዩ

/በግርምት እያያት/

እንዴት!?

ገነት

ዘመኑ ዘመነ ምህረት ስለሆነ

/የቀኝ እና የግራ እጇን መሀል ጣትና ሌባ ጣት አጣምራ እጥፍ ዘርጋ እያደረገች/

እንደ አማኞች አባባል oviously ፈጣሪ እነዚህን አረመኔ ጨካኞች ምንም ሊያደርጋቸው አይችልም

ነብዩ

/ትከሻውን ሰቅሎ/

እና

/መርከቡን ሙሉ ለሙሉ ወደ ነብዩ አሰጠጋችው/

ገነት

ታሪኩን ትንሽ ዞር ብናረገውስ መርከቡ ውስጥ ሀጥያተኞችን ከከተን እኛ ለምን ወደ እርሱ አንልክለትም ለሱም እረፈት ነው

## 3.1.4 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ከቃለ ፊልም አንጻር

ቃለ ፊልም በፊልም ጽሁፍ ውስጥ የተለያዩ ሚናዎች አሉት፡ ገጸ-ባህርያትን ለማሳወቅ ታሪክ ለመናገር፣ የገጸ-ባህርያትን ዝምድና ለማሳወቅ … ጥቅሞች አሉት፡፡ ከዚህ አንጻር የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍን ስንመለከት በአብዛኛው ገጸ-ባህርያቱ ሰብዕናቸውን ያሉበትን የዕውቀት ደረጃ እንዲሁም የስራ ሁኔታ የሚገልጽ ነው፡፡

ገጽ 5 ትዕይንት 4

ማታ ጭፈራ ቤት ውስጥ

ሮዛ

ሀይ

/አብርሀም ዝም ብሎአት ይጽፋል/

ሮዛ

ምን እየጻፍክ ነው?

አብርሀም

ከዛ ድረስ መተሽ ምን እየጻፍክ ነው እንደምትይኝ ነበር የምጽፈው

ሮዛ

ኧረረረረ

/እንደ መገረም እያለች/

እየሳልከኝ ነበር ግን የመሰለኝ

/አብርም አንገቱን በአሉታ እየነቀነቀ/

አብርሀም

ኖ እየደረስኩሽ ነበር ድርሰት ትወጃለሽ

ሮዛ

/ሳቅ እየተናነቃት/

እብድ

አብርሀም

/ፈገግ ብሎ አይቷት ቢራውን ተጎነጨ/

የሮዛ አቀራረብ አወራርዋ አሳሳቅዋ እራሷን የሚገልጽ ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የአብርሀም መልሶች ብልጣብልጥነቱን፣ አርቆ አሳቢነቱን የሚያሳይ ነው፤ ይህን ሁሉ ነገር በቃለ ፊልሙ

ውስጥ መመልከት ያስችለናል፡፡ እንዲሁም አንዱ ገጸ ባህሪ ከሌላኛው ጋር በሚነጋገርበት ሰዓት ስለአንደኛው ሰው ማንነት ይገልጽልናል፡፡

ገጽ 27 ትዕይን 33

ቀን ምርመራ ክፍል ውስጥ

አብርሀም

ለምሳሌ አንቺ

/ገነት ግር ተሰኝታ/

ገነት

እኔ?

አብርሀም

እህም! ሳይሽ የሆነ የሀብታም ልጅ ትመስያሽ

ገጽ 29

አብርሀም

ጎበዝ ተማሪ ነበርሽ ምን ተፈጠረ

በርግጥ እደ ማንኛውም የሀብታም ልጅ ፒኪ ነገር ነሽ ግን ለወንድ ያለሽ ጥላቻ ያኔ አልነበረም አትሊስት ይህን ያህል አልነበረም …!

/አብርሀም እጇ ላይ ያለውን ጠበሳ እያየ/

አብርሀም

ምን አልባት ከሱ ጠባሳ ጋር የተገናኘ ነገር ይኖረው ይሆን?

አብርሀም ከገነት ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ስለገነት የቤተሰቧን የኑሮ ደረጃ ስለ ትምህርት ጉብዝናዋ ለወንድ ስላላት ጥላቻ ከበፊቱ የባሰ የጥላቻ ስሜት ውስጥ እንዳለች እጅዋ

ላይ ጠባሳ እንዳለባት ይነግረናል፡፡ በዚህም መልኩ አንዱ ገጸ-ባህሪ ሌላውን ሊያስታውቅ ችሏል፡፡ እንዲሁም የሚናገሩት (የሚያደርጉት) ቃለ ምልልስ ሰብዕናቸውን ይገልጻል፡፡

ገጽ 12 ትዕይንት 12

ቀን መመርመርያ ክፍል ውስጥ

ኮማንደር

ምን መሆንህ ነው? ምን እያደረክ ነው?

ነብዩ

ኮማንደር … የሆነ … እልህክን እኮ ነው ሚያስጨርስህ

ኮማንደር

እሱም ይሄንኑ ነው የሚፈልገው አቅልህን አስቶ ከአቅጣጫ ማስወጣት

/ወደ ነብዩ ጠጋ ብሎ ትከሻውን በእጁ መታ መታ እያደረገው/

ወጥመድ ውስጥ አትግባለት እንጂ አርግተህ አድፍጥ

ከዚህ ቃል ምልልስ የኮማንደር በእድሜም ሆነ በልምድ ከነብዩ የተሻሉ እንዲሆኑ እንዲሁም ነብዩ ችኩል እና ቶሎ ተናዳጅ እንደሆነ ለመረዳት አስችሏል፡፡

እንደ አጠቃላይ በተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሙት አካባቢያዊ የሆነ እና ያልተወሳሰበ በዕለተ ዕለት ኑሮአችን የምንጠቀመው የቋንቋ አጠቃቀም ሲጠቀሙ ያሳያል፡፡ ቃለ-ፊልሙ ግልጽነት እና ተዓማኒነት ያለው ነው፡፡

## 3.1.5 የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ከሴራ አንጻር

የዚህ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ሴራ ወይም ለፊልሙ ጉዞት እንደመንስኤ ወይም እንደመነሻነት የምናነሳው የአብርሀም እህት (ርብቃ) ተደፍራ መሞትዋ፣ በዛም የተነሳ አብርሀም ውስጡ መጎዳቱ፣ ጎዳና ላይ ያለቅርብ ዘመድ በስቃይ ማደጉ፣ የእህቱ ገዳዮች በነጻነት መንቀሳቀሳቸው፤ የእነዚህ ሁሉ ነገሮች ጫና የአሁኑንን አብርሀምን ፈጠረው፡፡ አብርሀም

በጎዳና ልጆች እርዳታ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለመድረስ በቃ በዛም ከተፈጣሪዝም ፍልስፍና ባለቤት ጋር ተዋወቀ ስለ ተፈጣሪዝም ‹‹ቲዎሪ›› አብራርታ ስትነግረው በሂወቱ የጎደለበትን ፍትህ የሚያስገኝለት እንደሆነ ተሰማው በጣም ወደደው እራሱን ከተፈጣሪዝም ፍልስፍና ጋር ለማጣመር አስቦ የተፈጣሪዝምን ፈጣሪ በቅርበት አናግሯት ተስማሙም በተፈጣሪዝም ፍልስፍና የሂወቱን ሙሉ ችግር ለመፍታት ለራሱ በዛ መንገድ ፍትህ ለመስጠት ከገነት ጋር ረጅሙን ጉዞ አብረው ጀመሩት፤ በተፈጣሪዝም መንገድ መጓዝ ጀመሩ። አብርሀም ደርሶ የሚያዘጋጃቸው ፊልሞች ለህዝብ እይታ መቅረብ ጀመሩ። ከዛም የበዛ ዝናን አገኘ ሀብታምም ሆነ፤በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አገኘ። ያኔ የበደሉትን፣እህቱን የገደሉበት ሰዎች የሆነ ክስተት እንዲገጥማቸው በማድረግ የሚገባቸውን ቅጣት እየሰጠ ድርሰቱን መጻፍ ቀጠለ። ነገር ግን ወንጀሉ የሚፈጸምበት ቦታ በመገኘቱ እና የድርሰቱም ታሪክ ከሚፈጸመው የግድያ ወንጀል ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ምክንያት ክስ ይከፍትበታል ሆኖም ግን ወንጀሉን እሱ ለመፈጸሙ ምንም አይነት ማስረጃ ባለማግኘታቸው በነጻ ለቀውታል። ነገር ግን ያን ሁሉ ነገር ስታደርግ የነበረችው ገነት አባትዋ የአብርሀምን ሂወት ፍትህ ካሳጡት ሰዎች መሀከል አንዱ እሱ መሆኑን አታውቅም ነበር። በመመጨረሻም የእህቱ ገዳዮች በገነት አማካኝነት በሙሉ ተገድለው አብርሀም ፍትህ ለማግኘት የገነት አባትን መቅጣት ብቻ ቀረው። ገነት በፊት ስለተፈጣሪዝም ‹‹ታዎሪ›› ስታስረዳው አንድ ሰው ፍትህ ካጓደለ እራሱን መቅጣት ባይቻል እንኳን በልጁም ሆነ በልጅ ልጁ ብድሩን ማግኘት አለበት ብላው ነበር፣ ባለችውም መሰረት አብርሀም ገነት ወንጀሎቹን ስትገድል የሚያሳይ ቪድዮ ለፖሊሶች በመስጠቱ ወደ እስር ቤት ገባች።

የተፈጣሪ ፊልም (ስክርፕት) ላይ ያለው የሴራ አይነት ጥብቅ ሴራ የሚባለው  የሴራ አይነት ነው። በጥብቅ ሴራ ግዜ የተለያዩ ቁርጥራጭ ግጭቶችና የተለያዩ የሚመስሉ ታሪኮች ሁሉ በስተመጨረሻ ምክንያታዊነት በጠበቀ መልኩ መፍትሄ ያገኛሉ ወይም ይቋጫሉ። በዚህም መሰረት ታሪኩ የነበሩት ግጭቶች ሁሉ በአብርሃም ህይወት ፍትህ ማግኘት ምክንያት ሲቋጩ ያሳየናል።

### 3.1.6. የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ከጭብጥ አንጻር

የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ (ስክሪፕት) ጭብጥ አለማቀፋዊ (ዩንቨርሳል) የምንለው የጭብጥ አይነት ውስጥ ይመደባል። አለም አቀፋዊ ጭብጥ መሆን ከሚችሉ ነገሮች መሀል ክፍት፣ ደግነት፣ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ በቀል፣ፍትህ … ናቸው ይህ ‹‹ስክሪፕትም›› በውስጡ እነዚህን

አካቷል፡፡ ታሪኩም ወቅታዊና ግዚ የሚጥለው አይነት ስላልሆነ አለማቀፋዊ ጭብጥ ነው ለማለት ያስችላል፡፡

የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ዋናው ጭብጥ ፍትህ ነው፡፡ ፍትህ ያላገኘች ነፍስ እረፍት ፣ ሰላም እደሌላት ያሳያል፡፡ ለሰው ልጅ ሁሉ ፍትህ ይገባል ይላል፡፡ በፊልም ጽሁፉ ላይ አብርሀም ያጣውን ፍትህ ምንም እንኳን ህግን የጠበቀ ባይሆንም ፍትህን በማግኘቱ በድጋሚ ሂወቱ መስሩን ሊይዝ ወደ ደስታ ሲመለስ አይተናል፡፡ የተፈጣሪ ፊልም ‹‹ስክሪብት›› ፍትህ ምን ግዚም መስፈን እንዳበት ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.1. ማጠቃለያ

አጥኝው በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍን (ስክሪፕት) በጥልቀት እና በአስተውሎት በማየት ትንታኔ ሰጥቷል፡፡ አንድ የፊልም ጽሁፍ ‹‹ስክሪፕት› የተሳካና ያማረ እንዲሆን ህጎቹን ጠብቆ የተጻፈ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ የፊልም ጽሁፍ አላባውያን ለፊልሙ ጽሁፍ ‹‹ስክሪፕት›› የጀርባ አጥንት ናቸው፡፡ በሀገራችን የፊልም ‹‹ኢንዱስትሪ›› ከተጀመረ አንስቶ በርካታ ‹‹ ስክሪፕቶች›› በተለያየ ዘውግ ተጽፈዋል፡፡ ወንጀል ነክ፣ ታሪከ ቀመስ፣ የፍቅር፣ የህክምና አስቂኝ አሳዛኝ …. የመሳሰሉት ተጽፈዋል፡፡ ከነዛም መሀከል የተፈጣሪ ፊልም ተጠቃሽ ነው፡፡ ተፈጣሪ የፊልም ጽሁፍ ‹‹ስክሪፕት›› የጭብጡ አለም አቀፋዊ መሆን፣የገጸ-ባህሪያት ግንባታው፣ ቦታ መረጣው፣ የቃለ ፊልሙ መመጠን፣ ሴራው ፡ ለአንድ የፊልም ስክሪፕት ግብአትና ዋና የሚባሉት ነገሮች በደንብ የተተገበሩበት እና የተጻፈበት አጻጻፍ የፊልም ‹‹ስክሪፕት››አላባውያንን በተገቢው መንገድ ከመሟላት አንጻር እጅግ በጣም ጥሩ የሚባል ነው፡፡

## 4.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ የተፈጣሪ ፊልም ጽሁፍ ‹‹ስክሪፕት›› ከፊልም ጽሁፍ ‹‹ስክሪፕት›› አላባውያን አንጻር ለመመልከት ችሏል፡፡ በዚህም መሰረት ያሉትን ችግሮች ወይም ክፍተቶች ሊቀረፉ ወይም ሊሸፍኑ ይችላሉ ብሎ ያሰባቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች እደሚከተለው አስቀምጧል፡፡

በአሁን ወቅት በሀገራችን እየተጻፉ ያሉ የፊልም ጽሑፎች (ስክሪፕቶች) ጥሩና አበረታች ቢሆኑም፡፡ በሀገሪቱ ጥቂት ከተሞች ውስጥ የተጀመረው የስነ ጽሁፍ ትምህርት በተለያየ ቋንቋ በስፋት መስጠት ቢጀምር ዘርፉ ጥሩ እድገት እንደሚያሳይ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ለሀገራችን የስነ-ጽሁፍ እድገት መንግስት እና ህብረተሰቡ ዘርፉ ላይ በመስራት ጥበብን የማሳደግ ሀላፊነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እናም በዚህ የስነ-ጽሁፍ ዘርፍ ትኩረት ተደርጎ ከተሰራ የሀገራችን ባህል፣ወግ፣ጥሩ ልማዶች ከጥበቡ ጋር በማጣመር እንዲያድግ እና ለሌላው አለም እንዲታይ ያስችላል፡፡

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. Film is remarkably effective medium in conveying drama and especially in the evocation of emotion. The art of motion picture is exceedingly complex, requiring contributions from nearly all the other arts as well as countless technical skills (for example, in sound recording, photography, and optics)
2. The types of conflict list above can be divide in two internal and external conflict
    - Internal conflict

- Person VS self
    - External conflict
- Person VS GOD / fate
- Person VS society
- Person VS nature
- Person VS super natural
- Person VS technology

## ዋቢ መጽሀፍት


የሻው ተሰማ፡፡ 2009 ዓ/ም፡፡<u>ስነ-ተወኔት ግለ መማርያ፡፡</u>አዲስ አበባ፡፡ኢትዮ ከለር አሳታሚዎች፡፡

አለም እሸቱ፡፡ 1994 ዓ/ም፡፡ <u>የምርምር እና ዘገባ አጻጻፍ ዘዴ፡፡</u>አዲስ አበባ፡፡ የቅ/ማ ኮሌጅ ሬጉላር አርትስ ፋካልቲ፡፡

ኤልያስ ጋሻው፡፡  2007 ዓ/ም፡፡<u>ስኬታማ የፊልም አሰራር ከመደበኛው ህግጋት ባሻገር፡፡</u> ባህር ዳር፡፡ ነጭ ሳር ማተሚያ ድርጅት፡፡

ዘላለም ተፈሪ፡፡ 2010 ዓ.ም፡፡ <u>የፊልም ትወና ጥበብ</u> ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ 1994 ዓ/ም፡፡ <u>የስነጽሁፍ መሰረታዊያን፡፡</u> አዲስ አበባ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ጳውሎስ አዕምሮ፡፡ 2010 ዓ/ም፡፡ <u>የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ፡፡</u> አዲስ አበባ፡፡

ፈንታሁን እንግዳ፡፡ 2012 ዓ/ም ፡፡ <u>ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔአቸው፡፡</u> አዲስ አበባ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፈንታሁን እንግዳ፡፡ 2009 ዓ.ም፡፡<u>የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ፡፡</u> አዲስ አበባ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፕሮፌሰር ያለው እንዳወቀ፡፡ 2009 ዓ/ም፡፡ <u>የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና ተግባር</u>፡፡ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት

Justin CASH 2016.EC Elments of Drama( http:// thedramateacher.com/ elements-of-drama-conflict/

WWW.britannica.com    http:/www.britannica.com/art/motion-picture